# የነብዩ ﷺ አሰጋገድ

## ከተክቢር እስከ ተስሊም

«አሰጋገዴን እዳታችሁ ስገዱ፡፡» (ቡኻሪ ዘግበዉታል)


ዝግጅት፦ በሸይኽ ሙሀመድ ናስሩዲን አል-አልባኒ

ትርጉም፡- ኒዛሙዲን አወል


# تلخيصُ صِفة صلاة النّبي ﷺ

## من التكبير إلى التسليم كأنك تراها

«صلوا كما رأيتمُوني أصلي» رواه البخاري


إعداد: محمد ناصر الدين الألباني (رحمه الله تعالى)

ترجمة: نظام الدّين أوّل


أمهري – إثيوبيا

## ማውጫ


ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር ........ 5
የአሳታሚው መቅድም ........ 6
የተርጓሚው መቅድም ........ 7
የፀሐፊዉ አጭር የህይወት ታሪክ ........ 9

- የኢስላም ምሁራን ስለ አልባኒ ከተናገሩት ........ 10
- ለህትመት አበቁት መጽሐፎቻቸው በጥቂቱ ........ 11

መግቢያ ........ 12
ወደ ቂበላ (ካዕባ አቅጣጫ) መዞር ........ 14

- በስህተት ከካዕባ አቅጣጫ ውጪ ዞሮ መስገድ ........ 14

2.ቂያም ........ 14

- በመርከብ ወይም በአውሮፕላን ላይ መስገድ ........ 15
- ቆሞም ተቀምጦም መስገድ ........ 15

በጫማ መስገድ ........ 15
የኹጥባ መድረክ(ሚምበር) ላይ መስግድ ........ 16
ሱትራ አድርጎ መስገድ ........ 16

- የከለለው ከፍታ ልክ ........ 17
- ወደ ቀብር መስገድ ........ 17
- ከሰጋጅ ፊት ለፊት ማለፍ ክልክል መሆኑ ........ 17
- በሰጋጅ ፊት ለፊት ለማለፍ የሚፈልግ አካል እንዳያልፍ መከልከል ........ 18

በሰጋጅ ፊት ለፊት ለማለፍ የሚፈልግ አካል እንዳያልፍ ለመከልከል ወደፊት መራመድ ... 18
ሶላትን የሚቆርጡ ... 18

3.ኒያ ... 19
4.ተክቢረተል ኢህራም ... 19
እጆችን ማስቀመጥና የአቀማመጡ ሁኔታ ... 20
እጆችን የማስቀመጫ ቦታ ... 20
ኹሹዕ አና ወደ መስገጃ ቦታ ማየት ... 20
ዱዓኡል ኢስቲፍታህ ... 21
5.ቂራአ ... 21

ፋቲሀን መቅራት ... 21
የማዕሙም ፋቲሀ አቀራር ... 22
ከፋተሀ ቀጥሎ ተጨማሪ አንቀፆችን መቅራት ... 22
በያንዳዱ ረከዐ ላይ ፋቲሀን መቅራት ... 23
ድምፅን አሰምቶ ወይም ሳያሰሙ መቅራት ... 23
ቁርአንን አስውቦ መቅራት ... 23
ኢማም ሲሳሳት ማስተካከል ... 23

6. ሩኩዕ ... 24

የሩኩዕ አደራረግ ... 24

የእያንዳንዱ ማዕዘን ቀደታ ማቀራረብ ... 24
ከሩኩዕ መነሳት (ኢዕቲዳል) ... 24
7. ሱጁድ ... 25

እጅን አስቅድሞ ወደ ሱጁድ መውረድ ........ 25

ተስተካክሉ ሱጁድ ማድረግ ........ 26

8. በሱጁዶች መሀል ኢፍቲራሽ እና ኢቅዓዕ ........ 26

ሁለተኛው ሱጁድ ........ 27

ጀልስተል ኢስቲራሀ ........ 27

9. ሁለተኛ ረከዓ ........ 28

10. ለተሸሁድ መቀመጥ ........ 28

ጣትን ማንቀሳቀስ እና ጣቱንም መመልከት ........ 28

የተሸሁድ ይዘቱ እና ከተሸሁድ በኋላ ዱዓዕ ማድረግ ........ 28

11. ሦስተኛ እና አራተኛ ረከዓ ........ 30

12. የአደጋ ጊዜ ቁኑት (አል-ቁኑቱ ሊናዚል) ........ 30

13. የዊትር ቁኑት ቦታውና ይዘቱ ........ 30

14. የመጨረሻው ተሸሁድና እና ተወሩክ ........ 31

በነብዩ ﷺ ላይ ሰለዋት ማውረድ እና ከአራት ነገሮች አላህን ጥበቃ መለመን ........ 31

ከሰላምታ በፊት ዱዓዕ ማድረግ ........ 32

15. ሰላመታና አይነቶቹ ........ 32

በሶላት ዙሪያ የሚያውጠነጥኑ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........ 34

نبذة تعريفية عن مركز ابن مسعود الإسلامي ........ 51

# ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

በሰኔ ወር 2001ዓ.ል ተመስርቶ በተቀናጀ መልኩ ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።

<u>የማዕከሉ ዋና ዋና ክፍሎች</u>

- የዓረብኛ ቋንቋና የሸሪዓዊ ጥናቶች ኢንስቲትዩት (ለሴቶች)
- የሙሉ ቀን የቁርዓን ሒፍዝ መጅሊስ (ለሴቶችና ለወንዶች)
- ኢስላማዊ የቤተ መፃህፍት አገልግሎት
- የህፃናት ኢስላማዊ የተርቢያ ማዕከል
- የመድረሳዎች ድጋፍ መስጫ እና የካሪኩለም ማሻሻያ
- የኢንተርኔት ዳዕዋ ማዕከል
- መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ ትምህርት
- ሙስሊም ላልሆኑና በቅርቡ ለሰለሙ መሰረታዊ ትምህርት
- ለዲን ተማሪዎች መደበኛ ያልሆነ የአካዳሚ ትምህርት
- የተለያዩ ኪታቦች ቂራዓት ለወንዶችና ለሴቶች
- የተለያዩ ኮርሶች፣ ሴሚናሮች እና ኮንፈረንሶች
- የካሴቶች፣ ሲዲዎችና የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች ስርጭት
- የመስጅዶች ግንባታ
- የኡስታዞች ድጎማ
- የወቅፍ ማስተባበርያ

**<u>የማዕከሉ አድራሻ</u>**
☏ +251112781893
Fax: +251112779660
e-mail:-info@nesiha.org
www.nesiha.org
<u>አዲስ አበባ</u>
<u>ኢትዮጵያ</u>

# የአሳታሚው መቅድም

የኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር ከተመሠረተበት ዓላማ አንዱ **ቁርአንና** ትክክለኛ **ሀዲስን** መሠረት ያደረጉ ኢስላማዊ መፃህፍትን በሀገራችን በሰፊው በሚነገሩ ቋንቋዎች በማዘጋጀትና በመተርጎም ማ ቅረብ ሲሆን፤ ይህንንም **የነብዩ ﷺ አሰጋገድ** የሚል ርዕሥ ያለውን መፀሃፍ ለአንባቢያን ሲያቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል:: አንባቢያን በመፅሃፉ ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት እንዲጠቁሙ እየጠይቅን ባወቅነው የምንጠቀም ያደርገን ዘንድ አላህን እንለምነዋለን::

# የተርጓሚው መቅድም

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

የሁሉም ፈጣሪ እና ሁሉንም ተንከባካቢ ለሆነው የአለማት ጌታ አላህ ምስጋና ተገባው ፡፡ የነቢያቶችና የመልዕክተኞች መሪ በሆኑት በነቢያችን ሙሀመድ ﷺ በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በሁሉም ባልደረቦቻቸው ላይ የአላህ ሶላት እና ሰላም ይስፈን ፡፡ ሶላት፡- ከስራዎች ሁሉ በላጭ፤ የዲን ምሰሶ፤ የሙዕሚኖች አይን ማረፊያ፤ የሙስሊሞች መለያ ምልክት፤ አዛኝ የሆነው ጌታ ትዕዛዝ እና የምርጡ ነብይ ﷺ ኑዛዜ ነው፡፡

ሶላት ተቀባይነት እንዲኖረው እና የተሟላ ምንዳ ያስገኝ ዘንድ ደንቡና ህግጋቱ ተሟልቶ ነብዩ ﷺ ሲሰግዱ በነበረው መልክ መሰገድ አለበት ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ኢማሙ አህመድ በዘገ ቡት ሀዲስ፡- «አንድ የአላህ አገልጋይ (ባሪያ) ከስግደቱ (ምንዳ) አንድ አስረኛ፤ ወይም አንድ ዘጠነኛ፣ ወይም አንድ ስምንተኛ... ወይም አንድ ሁለተኛ እንጂ ላይመዘገብለት ይችላል ፡፡» በማለት ስርዓቱ ተጠብቆ ያልተሰገደ ሶላት የተሟላ ምንዳ እንደማያስገኝ ገልጸዋልና ፡፡ በተጨማሪም ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ **«አሰጋገዴን አይታችሁ ስገዱ፡፡»** በማለት የሳቸውን የአሰጋገድ ስርዓት መከተል ግዴታ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡ ስለሆነም የታላቁን የአላህ መልዕክተኛ ﷺ የአሰጋገድ ስርዓት መማር አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ ነው ፡፡ ይህን ዕውቀት የምንገበይባቸው የተለያዩ መንገዶች ቢኖሩም፤ በተለይ ብዙ ሰዎች ለዲን እዉቀታቸው ጊዜ ሰጥተው መስጊድ በመቀመጥ መማር በተዉበት በአሁኑ ጊዜ፤ መፅሐፍት -በቀላሉ ልናገኛቸዉ፤ በየትኛዉም ቦታ ልንጠቀምባቸዉና በብዛትም የሶስተኛ ወገን እርዳታን የማይሹ በመሆናቸዉ - ጥሩ የእዉቀት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በሰላት ዙሪያ ምንም እንኳ በአረብኛ ቋንቋ የተፃፉ ብዙ መፅሐፍት ቢኖሩም አያሌ የሀገራችን ህብረተሰብ የአረብኛ ዕውቀቱ ውስን በመሆኑ ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም ፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ትርጉም ማቅረብ ለዚህ አሳሳቢ ችግር መጠነኛ መፍትሄ መስጠቱ አጠያያቂ አይደለም ፡፡

ይህን ከግንዛቤ በማስገባት «ተልኺሱ ሲፈቲ ሶላቲ ነቢይ ﷺ ሚነ ተክቢሪ ኢለ ተስሊም » በሚል ርዕስ በታላቁ የኢስላም ምሁርና የሀዲስ ሊቅ ሸይክ ሙሀመድ ናስሩዲን አል -አልባኒ የተዘጋጀውን መፅሀፍ ለመተርጎም ተነሳሁ፡፡ ይህንም መፅሀፍ የመረጥኩበት ዋነኛው ምክንያት አጠር ያለ፤ ብዙ ጠቃሚ ነጥቦችን ያዘለ፤ አቀራረቡ ቀላል እና ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችል በመሆኑ ነው ፡፡ ጸሀፊው ይህን መፅሐፍ በመጀመሪያ በሶስት ትላልቅ ተከታታይ ጥራዞች አዘጋጅተው ዝርዝር መረጃዎችን አካትተው ካቀረቡ በኋላ ቀላል እንዲሆንና በስፋት የዲን ተማሪዎች እንዲጠቀሙበት በማሰብ ወደ አንድ ጥራዝ

አሳጠሩት። በኋላም ብዙሃን ከመፅሐፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጉጉት ስላደረባቸው በጣም ቀላልና አጭር በሆነ አቀራረብ በዚህ መልክ አሳጥረው አዘጋጁት ።

በተጨማሪም የመጽሐፍቱን ጠቀሜታ ይበልጥ ያጎለብተው ዘንድ በሶላት ዙሪያ በተለይ በአሰጋገድ ዙርያ የሚያጠነጥኑ በእውቅ ዓሊሞች (ኢብን ባዝ፣ ኡሰይሚን እና የሳኡዲ አረቢያ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ) የሰጡትን ፈትዋዎች ከተለያዩ መጻህፍት በመምረጥ በመጽሃፉ መጨረሻ ላይ አካትቻለሁ ። መጽሀፉ የአሰጋገድ ህግጋትን ብቻ የያዘ በመሆኑ የሰላትን ትሩፋቶች በማብራራት ጽናትን ለማሳደግ እና ቀልብን ለመግራት የሚጠቅም "ጥሪ ወደ ሰላት" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ መጽሀፍ በመተርጎም ለንባብ ያበቃሁ ሲሆን አንባቢያን ሁለቱንም መጽሀፎች በማንበብ አንዱን በአንዱ እንዲያሟሉ አደራ እላለሁ።

በዚህ ትርጉም ስራ የመጽሐፉን መልዕክት ይዘቱን ሳልለውጥ ለማስተላለፍ ጥረት አድሪጊያለሁ ። ይሁን እንጂ በስራው ዉስጥ ግድፈቶች ሊኖሩበት ይችላልና የአንባቢያን አስተያየት እና እርምት እንዳይለየኝ አደራ እላለሁ። መጽሀፉን አዘጋጅቶ በማሣተሙ ሂደት ትብብር ያደረጉልኝን ሁሉ ሳላመሰግን አላልፍም። አላህ ይህንን ስራዬን የእርሱን ምንዳ ብቻ ተፈልጎ የተሰራ እና ለአንባቢያን ጠቃሚ ያደርገው ዘንድ እማጸነዋለሁ ። አላህ የሰላትን ደንብና ስርዓት ጠብቀን ነብዩ ﷺ ሲሰግዱት እንደነበረው- የምንሰግድ ያድርገን።

ኒዛሙዲን አወል
አድራሻ:- E-mail:- rehu2000@gmail.com፣ nizawol@yahoo.com
ረመዳን 1431 ዓ.ሂ

# የፀሐፊዉ አጭር የህይወት ታሪክ

ሙሀመድ ናስሩዲን አል -አልባኒ ከደሃ ቤተሰብ የቀድሞው የአልባኒያ ዋና ከተማ በነበረችው ችኮድራ በ1332ዓ.ሂ(1914 G.C) ተወለዱ። አባታቸው ሀጅ ኑህ ነጃቲ አል -አልባኒ የኢስላምን ህግ (ሸሪዓ) በኢስታምቡል ያጠኑ የአልባኒያ ምሁር ነበሩ ። ቤተሰቦቻቸውም በጊዜው በአልባኒያ በነበረው አለማዊ (Secularist) መንግስት አስተዳደር ባለመስማማታቸው ወደ ደማስቀ ተሰደዱ ። በደማስቆም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ ። በተጨማሪም ቁርዓን፣ የቁርዓን አነባብ ሰርዓት (ተጅዊድ)፣ የአረብኛ ቋንቋ፣ የሃነፊያ መዝሀብ እና ሌሎች ተዛማች የሃይማኖት ትምህርቶችን የአባታቸው ጓደኞችን ጨምሮ ከተለያዩ የኢስላም ምሁሮች ተማሩ።

ሙሀመድ ናስሩዲን አል -አልባኒ ከአባታቸው የሰዓት ጥገና ሙያን ተምረዋል ። በንግድ ስራም በጣም የተካኑ ነበሩ ። 20 ዓመት ሲሞላቸው በሀዲስ እና ተዛማች ትምህረቶች ጥልቅ ጥናት (specialization) ማድረግ ጀምሩ ። አባታቸው ቀለል ያለ የትምህርት ዘርፍ እንዲያጠኑ በመፈለግ የሀዲስ ጥናታቸውን ቢያጣጥሉባቸውም አልባኒ ግን ፅኑ ፍላጎታቸው መሆኑን ገለጹ ። የሀዲስ ጥናታቸውንም የተለያዩ መጽሐፍቶችን በመግዛትና መግዛት ያልቻሉትን ከታዋቂው ደማስቆ ውስጥ ከሚገኘው አዝ -ዛሂሪያህ ኢስላማዊ ቤተ -መፅሐፍት በመዋስ በስፋት ቀጠሉበት ። በስራቸውም በጣም በመመሰጣቸው አንዳንዴ ሱቃቸውን ዘግተው ፈሳሽ ምግብ ብቻ ይዘው ለ 12 ሰዐታት ያህል (ለሰላት ብቻ እየወጡ ) በቤተ-መፅሐፍት ውስጥ ይቆዩ ነበር ። ይህን የንባብ ፍቅራቸዉን የተገነዘቡት የቤተ -መፅሐፍቱ ሀላፊዎች አልባኒ በፈለጉት ሰዓት ገብተው እንዲያነቡ የቤተ -መፅሀፍቱን የበር ቁልፍ እና ምቹ የሆነ ልዩ የንባብ ክፍል ሰጧቸው ። ከጧት ጀምሮ እስከ ኢሻዕ ሶላት ድረስ በዚሁ ቤተ -መጻህፍት ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን እየሰሩ መቆየት ጀምሩ። በዚህም ወቅት አብዛኛው ያልታተመ በርካታ ጠቃሚ ስራዎችን ለህብረተሰቡ አበረከቱ ። ለህትመት የበቁ ከ 70 የሚበልጡ ባለ አንድ እና ባለ ብዙ ጥራዝ መጻህፍትን ለሙስሊሙ ህብረተሰብ አበርክተዋል። ከተወሰነ ጊዜ በኂላም የተለያዩ የአቂዳ፤ ፊቂህ፣ ኡሱል እና ሀዲስ መጽሐፍቶችን በየሳምንቱ ለሁለት ሰዓታት ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ፕሮፌሰሮች ማስተማር ጀመሩ ። ወርሃዊ የዳዕዋ ጉዞ ወደ ተለያዩ የሶሪያና የጆርዳን ከተሞች እንዲደረጉ ያስተባብሩም ነበር።

ብዙ ስራዎቻቸው ከታተሙ በኂላ በመዲና ኢስላሚክ ዩኒቨርስቲ የሀዲስ መምህር እንዲሆኑ ተመረጡ ። ለሶስት ዓመታትም (ከ1981-1383 ዓ.ሂ) የዩኒቨርስቲው የመምህራን የቦርድ አባል በመሆን አገለገሉ ። በኂላም ወደ ሀገራቸው በመሄድ በወቅቱ የነበራቸውን ሱቅ ለወንድማቸው በመስጠት ወደ ቀድሞው የአዝ -ዛሂርያህ ቤተ መጽሐፍት ጥናታቸው ተመለሱ።

አል-አልባኒ ደዕዋ በማድረግና በማስተማር ብዙ ሃገራትን ጎብኝተዋል ። ከነዚህም ውስጥ ኳታር፣ ግብጽ፣ ኩዌት፣ የተባበሩት አረብ ኤሜሬት፣ ስፔን እና እንግሊዝ ተጠቃሾች ናቸው ። አብዛኛውን በሀዲስና ተጓዳኝ

በሆኑ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ወደ 100 የሚሆኑ የተለያዩ የጽሁፍ ስራዎችን ለሙስሊሙ ማህበረሰብ አበርክተዋል። ከዚህም ውስጥ 70 ያህሉ ለእትም በቅቷል ። ብዙ ታዋቂ ተማሪዎችንም አፍርተዋል ። ከነዚህም ውስጥ ሸይክ ረቢዕ ኢብን ሃዲ አል መድኸሊ፣ ሸይክ ሀምዲ አብዱል መጂድ፣ ሸይክ ሙቅቢል ኢብን ሃዲ ፣ ሸይክ ሙሀመድ ጀሚል ዘይኑ፣ ሸይክ አሊ ሀሰን አብዱልሀሚድ አል-ሀለቢ እና ሸይኽ መሽሁር ሀሰን ሰልማን ጥቂቶቹ ናቸው።

አላህ ይዘንላቸውና እኚህ ተተኪ ያልተገኘላቸው የዘመናችን የሀዲስ ምሁር በ88 አመታቸው በ1420 ዓ.ሂ (1999 G.C) ከዚህች አለም በሞት ተለዩ።

## የኢስላም ምሁራን ስለ አልባኒ ከተናገሩት

★ አልባኒ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላቁ የኢስላም ምሁር ነው።

(ከአብዛኛዎቹ ምሁሮች)

★ "አልባኒ ሀቅን የሚረዳ እና ባጢልን የሚጋፈጥ የሱና ሰው ነው"

(የቀድሞ የሳዑድ አረቢያ ሙፍቲ ሸይኽ ሙሀመድ ኢብራሂም አል ሸይኽ)

★ "ሸይኽ አልባኒ ከሱና ተጣሪዎችና ረዳቶች ሀዲስን ጠብቆ ለማቆየት ታላቅ ተጋድሎ ከሚያደርጉ ሙጃሂዶች አንዱ ነው።" (አብዱል-አዚዝ ኢብን ባዝ)

★ "በዘመናችን በሀዲስ እውቀት ታላቁን ሙሀመድ ናስሩዲን አል -አልባኒ የሚያክል ሰው አላየሁም ።" (አብዱል-አዚዝ ኢብን ባዝ)

★ "ከሸይኽ አልባኒ ጋር በአካል ካደረኳቸው ጥቂት ቆይታዎች የተረዳሁት ሱናን ለመተግበር እና የእምነትንም ይሁን የተግባር ቢድዓዎችን ለመዋጋት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ነው። መጽሀፍቶቻቸዉን በማንበብም ይህንንኑ ተረድቻለሁ። በተጨማሪም የሀዲስን ሰነድ እና ቃላት በጥልቀት የሚያዉቁ ከመንሀጅም አንጻር ታላቅ ሰው ሲሆኑ ሰዎች ወደ ሀዲስ ጥናት እንዲዞሩ በማድረግ ረገድ በመጽሀፍቶቻቸው አላህ ብዙ ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።ይህ ደግሞ ለሙስሊሞች ታላቅ ዉጤት ነው። አላህ የተመሰገነ ይሁን"

(ታላቁ አሊም ሙሀመድ ቢን ሳሊህ አል-ዑሰይሚን)

★ "አልባኒ... በሀዲስ የእዉቀት ዘርፍ እጅግ ሰፊ የሆነ እውቀት ባለቤት ነው"

(ታላቁ ሙሀዲስ ሀማድ አልአንሷሪ)

★ ሼይክ ሙሀመድ ናስሩዲን አል-አልባኒ ብርቅዬና ልዩ ተሰጥኦ ካላቸው የዘመናችን ታላላቅ ምሁሮች አንዱ ናቸው።

(ዚያድ ኢብን ፈያድ)

★ የመልዕክተኛው ፈለግ (ሱና) ዳግም ሕይወት እንዲዘራ ሙሉ ሕይወታቸውን ከሰጡት ሰዎች ውስጥ አንዱ ወንድማችን ሙሀመድ ናስሩዲን አል-አልባኒ ነው፡፡

(ሙሂቡዲን አል-ኸጢብ)

★ በዚህ ዘመን አልባኒ የሱና ምልክት ሆነዋል

(ሸይኽ ሀሙድ አቱወይጂሪይ)

★ አልባኒ ሱናን ያገለገለ ታላቅ አሊም ነው፡፡ አቂዳዉም መልካም ነዉ… በእውነቱ አልባኒ በዚህ ዘመን ልዩ ከሆኑ እና ሱናን ከማገልገል አንጻር ልዩ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ኡለማዎች አንዱ ነው፡፡

(ሸይኽ አብዱልሙህሲን አል ዓባድ)

## ስህተመት ከበቁት መጽሐፎቻቸው በጥቂቱ

- ሲፈቲ ሶላቲ ነቢይ ﷺ ሚነ ተክቢር ኢለ ተስሊም (የነብዩ የሰላት አሰጋገድ)
- አት-ተርጊብ ወት-ተርሂብ (ከቅጽ 1-4)
- አት-ተስፊያህ ወት-ተርቢያህ
- ሰሂህ ወደኢፍ ሱነን አቢዳውድ (ከቅጽ 1-4)
- ሰሂህ ወደኢፍ ሱነን ኢብን ማጃህ (ከቅጽ 1-4)
- ሰሂህ ወደኢፍ ሱነን ቲርሙዚይ (ከቅጽ 1-4)
- አል-አቂደቱ ጠሃዊየህ (ሸርህ ወት-ተዕሊቅ)
- ሲልሲሊቱል አሀዲስ አስ-ሰሂሀህ (ከቅጽ 1-11)
- ሲልሲለቱል አሀዲስ አዶኢፍህ (ከቅጽ 1-14)
- ሶላቱ ተራዊህ
- አህካሙል ጀናኢዝ (የቀብር ስርዓቶች)
- አዳቡ ዘፋፍ (የጋብቻ ስርዓቶች)
- አተወሱል አንዋዑሁ ወአህካሙሁ (የተወሱል አይነቶችና ብይኖቻቸው)
- ተህሪሙ ኣላቲጠረብ (የሙዚቃ መሳሪያዎች ሀራምነት)

# መግቢያ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ለአላህ ተገባው ፡፡ እናመሰግነዋለን፤ እገዛን እንጠይቀዋለን፤ ምህረትን እንለምነዋለን ፡፡ ከነፍሶቻችን ጥፋት እና ከክፉ ተግባራችን በአላህ እንጠበቃለን ፡፡ አላህ የመራውን ማንም አያጠመውም፤ የጠመመን ወደ ቅን መንገድ የሚመራው የለም ፡፡ ከአላህ ሌላ የሚመለክ አለመኖሩን፣ ብቸኛ እና አጋር የሌለው መሆኑን፤ ሙሀመድም ﷺ አገልጋዩና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ ፡፡

ብዙ ወንድሞቼና ጓደኞቼ «ሲፈቲ ሶላቲ ነቢይ ﷺ ሚነ ተክቢር ኢለ ተስሊም » የሚለውን መፅሀፌን መልዕክቱ ለማንኛውም ሰው ግልፅ በሆነ መልኩ እንዳቀናጀው እና ይዘቱን እጥር ምጥን አድርጌ እንዳቀርበው አስተያየት ሰጥተውኝ ነበር ፡፡ ይህን አስተያየት መልካም ሆኖ በማግኘቴ እና በውስጤ ሲመላለስ ከነበረው ሀሳብ ጋር በመጣጣሙ በኢልም ስራ ከተጨናነቀው ጊዜዬ ትንሽ በመቀነስ ስኬታማነቱ ልዑልና ከጉድለት የጠራው ጌታዬ የእርሱ ምንዳ ብቻ ተፈልጎ (በኢኽላስ) የተሰራ እና ሙስሊም ወንድሞቼንና እህቶቼን የሚጠቅም እንዲያደርገው በመለመን የአቅሜን ያህል ለመስራት ተቻኮልኩ ፡፡
በቀድሞ መጽሀፍ ያልተካተቱ እና ጥቅም ያስገኛሉ ብዬ የገመትኳቸውን አንዳንድ ተጨማሪ ነጥቦች አካትቻለሁ፡፡ አንዳንድ ጥቅል በሆነ ሀዲስ የተገለፁ ቃላትን እንዲሁም ውዳሴዎችን (አዝካርችን) በማብራራት ልዩ ትኩረት ሰጥቻቸዋለሁ፤ ለያንዳንዱ ክፍል ዋና ርዕሶችን በማድረግ ከርዕሶቹም ስር በዛ ያሉ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ በማሰብ ንዑስ ርዕሶችን አድርጊያለሁ፤ እያንዳንዱንም ነጥብ በተከታታይ በቁጥር አስፍሪያቸዋለሁ፡፡ በተጨማሪም **ማዕዘን** (ሩክን)፣ **ግዴታ** (ዋጂብ) በማለት ከያንዳንዱ ነጥብ ጎን **ሁክሙን** (ፍርዱን) አብራርቻለሁ፡፡ ሁክሙን ከመግለጽ የተቆጠብኩት ሁሉ **ሱና** ነው ፡፡ ሱና ወይም ዋጂብ መሆናቸውን በእርግጠኝነት ለመናገር አዳጋች የሆኑ ነጥቦችንም ከመግለጽ ተቆጥቢያለሁ ፡፡
**ሩክን (ማዕዘን)፦** ማንኛውም ስራ ማዕዘኑ ከተሟላ ስራው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ማዕዘኑ ካልሟላ ግን ያ ስራ ውድቅ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፦ ሩኩዕ የሶላት ማዕዘን ነው፡፡ ሰጋጁ ሩኩዕን ካጓደለ ሰላቱ ውድቅ ይሆናል፡፡
**ሸርጥ (ቅድመ-ሁኔታ)፦** እንደ ማዕዘን ሆኖ ነገር ግን የዋናው ተግባር አካል አይደለም፡፡
ለምሳሌ፦ ውዱዕ የሶላት ሸርጥ ሲሆን ያለ እሱ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም ፡፡ (ነገር ግን ዉዱዕ የሰላት አካል አይደለም፡፡)
**ዋጂብ (ግዴታ)፦** በሀዲስ እና በቁርዓን የመጣ ትዕዛዝ ሆኖ ማዕዘን ወይም ቅድመሁኔታ ለመሆኑ መረጃ ያልተገኘለት ሲሆን የተገበረው ይመነዳል ፡፡ ያለ አሳማኝ ምክንያት (ዑዝር) የተወው ይጠየቅበታል ፡፡ከፈርድ ጋር አንድ አይነት ትርጉም አለው፡፡ የተለያዩ ለመሆናቸው መረጃ የለም፡፡

**ሱና፡-** መልዕክተኛው[1] ﷺ አብዛኛውን ጊዜ ወይም ሁል ጊዜ ጌታቸውን የሚያመልኩበት ተግባር ሲሆን በግዴታነቱ ያላዘዙት ነው ። የተገበረው ይመነዳል፤ የተወው አይቀጣም ወይም አይወቀስም ። አንዳን ሰዎች (ሱናን የተወ ምልጃ እንደማያገኝ መረጃ አድርገው የሚያቀርቡት ) ***«መንተረከ ሱነቲ ለንተንፈአሁ ሸፋአቲ፡»*** ማለትም፡- ***«ሱናዬን የተወ ምልጃዬ አይጠቅመውም ።»*** የሚለው ሐዲስ የመልዕክተኛው ﷺ ንግግር ለመሆኑ ማረጋገጫ አልተገኘም (ሰሂህ አይደለም)። መልዕክተኛው ﷺ ያልተናገሩትን ወይም ያልተረጋገጠ ወሬን መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ብለዋል ብሎ መዘገብ በጣም የተወገዘ ተግባር ነው ። መልዕክተኛውም ﷺ ***«እኔ ያልተናገርኩትን እንደተናገርኩ አድርጎ በማውራት በኔ ላይ የዋሸ መቀመጫውን እሳት ውስጥ ያዘጋጅ »*** በማለት የወንጀሉን ክብደት ገልጸዋል።

እዚህ ላይ ግልፅ አድርጌ መናገር የምፈልገው በዋነኛው መፅኃፌም ሆነ በዚህኛው ከአራቱ መዝሀቦች የትኛውንም በተናጠል አልተከተልኩም ። እኔ የተከተልኩት እነዚያ ትክክለኛ የመልዕክተኛው ﷺ ንግግር ሲመጣላቸው የሚቀበሉ የሆኑትን የሃዲስ ባልተቤቶች (አህሉል ሃዲስ) መንገድ ነው። የእነሱም መንገድ (የመልዕክተኛውን ﷺ ትክክለኛ ንግግር ብቻ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ) ከሌሎች መዝሃቦች የተሻለና ጠንካራ ነው። በዚህ እውነታ ላይም የየትኛውም መዝሃብ ተከታዮች መስክረዋል ። ከነዚህም ውስጥ አቡ ሀሰናት ሊል-ከንዊይ የሃነፊያ መዝሃብ ተከታይ የሆኑት አንዱ ናቸው ። እንዲህ በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ***«እንዴታ እነሱ የመልዕክተኛው ﷺ ወራሽ፤ እውነተኛ የህግጋቱ (ሸሪዓ) ተወካይ ሆነው ሳሉ። አላህ በትንሳዔ ቀን ከነሱ ጋር ይሰብስበን ። በነሱ ውዴታና መንገድ ላይ ሳለንም ህይወታችን ትለፍ ።»*** ኢማሙ አህመድ ኢብን ሀምበልም (አላህ ይዘንላቸውና) ይህን በተመለከተ ጥቂት ስንኞችን ቋጥረው ነበር። ትርጉሙን እንሆ፤

***የሙሀመድ ﷺ ሀይማኖት ንግግሩ ሀዲሶቹ *** ለወጣቱ ምንኛ ያማረው መንገድ ፋናዎቹ ከሀዲስ እና ከባልተቤቶቹ ውጪ ምንም አትሻ *** ሎጂክ ሌሊት ሲሆን ሀዲስ ግን ብርሃን ነው ወጣቱ የቅናቻን መንገድ ፋና ማወቅ ተስኖታል *** ፀሃይ ወጥታ ብርሃኗን ፈንጥቃ ሳለች***

*ሙሀመድ ናስሩዲን አል-አልባኒ*
*ደማስቆ- ሰፈር -26 -1392 ዓ.ሂ. (1963 ዓ.ል)*

---

[1] ይህ ቃል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በሁሉም ቦታዎች ላይ የሚያመለክተው ነብዩ ሙሀመድን ነው ። ከአጠገቡ በአረብኛ የሚቀመጠው ምልክትም "የአላህ ሰላምና እዝነት በእርሳቸው ላይ ይሁን" ማለት ነው።

# ወደ ቂበላ (ካዕባ አቅጣጫ) መዞር

1. አንተ ሙስሊም ሆይ! ሶላትን ለመስገድ በተነሳህ ጊዜ ባለህበት ቦታ ሆነህ በፈርድም ሆነ በሱና ሶላቶች ወደ ቂብላ ዙር። ይህም ከሶላት ማዕዘናት አንዱ ነው። ሶላት ያለ እሱ ተቀባይነት የለውም።
2. **ወደ ቂብላ መዞር ግዴታ የማይሆንባቸው ሁኔታዎች፡**

★ የፍራቻ ሶላትን (ሶላተል ኸውፍ) ለሚሰግድ እና በብርቱ ጦርነት ላይ ላለ፤

★ **ወደ ቂብላ መዞር የማይችል፡-** ለምሳሌ በሽተኛ ሰው፣ በመርከብ፣ በመኪና ወይም በአውሮፕላን ላይ እየተጓዘ ሳለ የፈርድ ሶላት ወቅት ያልፈኛል ብሎ የፈራ

★ በእንስሳት ወይም በሌላ መጓጓዣ እየሄደ ሱናን ወይም ዊትርን የሚሰግድ ሰው ተክቢረተል ኢህራም[2] ሲያደርግ -ከተመቻቸው- ወደ ቂብላ ቢዞር ይወደዳል። ከዚያም ወደ ሚጓዝበት አቅጣጫ ይዞራል።

3. ካዕባ አጠገብ ሆኖ ካዕባን ለሚመለከት ቀጥታ ወደ ካዕባ ዞሮ መስገድ ግዴታው ሲሆን ካዕባ አጠገብ ለማይገኝ ደግሞ ወደ አቅጣጫው ይዞራል።

### በስህተት ከካዕባ አቅጣጫ ውጪ ዞሮ መስገድ

4. በደመና ወይም በሌላ ምክንያት ቂብላ ጠፍቶበት አቅጣጫውን ለማግኘት የተቻለውን ያህል ጥረት አድርጎ (ሳይሳካለት) ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞሮ ቢሰግድ ሰላቱ በቂ ነው። መድገም አይጠቅበትም።
5. እየሰገደ ሳለ ታማኝ የሆነ ሰው መጥቶ ትክክለኛውን አቅጣጫ ካመላከተው -ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ- ፈጥኖ መዞር አለበት።

# 2.ቂያም

6. ቆሞ መስገድ ግዴታ (ዋጂብ) እና ከሶላት ማዕዘን(ሩክን) ነው።ለሚከተሉት ሲቀር፡-

◆ በብርቱ ጦርነት ላይ፣ የስጋት ሰላት «ሶላተል ኸውፍ» የሚሰግድ ሰው፡- እየጋለበ መስገድ ይፈቀድለታል።

◆ **መቆም የማይችል በሽተኛ የሆነ ሰው-** ከቻለ ቁጭ ብሎ ካልሆነም ተጋድሞ መስገድ ይችላል።

◆ **ሱናን የሚሰግድ ሰው** ፡- በመጓጓዣው እየተጓዘ፤ ከፈለገም ቁጭ ብሎ መስገድ ይችላል ። ጭንቅላቱን በማጎንበስ ሩኩዕን እና ሱጁድን ያደርጋል ። በሽተኛም ከሆነ እንዲሁ- ሱጁዱን ከሩኩዕ አንጻር ዝቅ ያደርጋል።

7. ተቀምጦ ለሚሰግድ ሰው ሱጁድ ለማድረግ በመሬት ላይ ከፍ ያለ ነገርን ማስቀመጥ አይችልም ። ጭንቅላቱን መሬት አስነክቶ ሱጁድን ማድረግ ካልቻለ -ከላይ እንደ ተጠቀሰው- ሱጁዱን ከሩኩዑ ዝቅ አድርጎ በማጎንበስ ይሰግዳል።

---

[2] የሶላት መግቢያ የሆነው የመጀመሪያው ተክቢራ

### በመርከብ ወይም በአውሮፕላን ላይ መስገድ

8. በመርከብም ሆነ በአውሮፕላን ላይ የፈርድ ሶላቶችን[3] መስገድ ይቻላል፡፡
9. ቆሞ ለመስገድ መውደቅን ከፈራ ቁጭ ብሎ መስገድ አለበት ፡፡
10. ሽማግሌ ሆኖ አቅም ካጣ ወይም አካሉ ከደከመ ምርኩዝ አልያም ምሰሶ ተደግፎ መቆም ይችላል ፡፡

### ቆሞም ተቀምጦም መስገድ

11. የሌሊትን ሶላት (ዊትር) ያለ ምንም ምክንያት (ዑዝር) ቆሞ፣ ተቀምጦ፤ ወይም እያፈራረቀ (ቆሞም ተቀምጦም) መስገድ ይችላል ፡፡ (ለምሳሌ) በመጀመሪያው ረከዓ ላይ ቁጭ ብሎ ቁርዓንን ማንበብ ይጀምራል፡፡ ከዚያም ሩኩዕ ሳያደርግ ይቆምና መቅራቱን ይቀጥላል፤ የሚቀራውን ሲጨርስ ሩኩዕ ከዚያም ስጁድ ያደርጋል፡፡ በሚቀጥለውም ረከዓ በእንደዚሁ አይነት ይቀጥላል ፡፡
12. ቁጭ ብሎ ሲሰግድ እግሩን አደራርቦ ወይም ሌላ በሚመቸው አይነት አቀማመጥ ይቀመጣል ፡፡

## በጫማ መስገድ

13. በባዶ እግሩ መስገድ እንደሚችለው ሁሉ ከነጫማውም መስገድ ይችላል ፡፡
14. በላጩ ሁለቱንም እንደ ተመቸው እያፈራረቀ መጠቀሙ ነው ፡፡ ይህ እንዳይሆን የሚያደርግ ሁኔታ እስካልተከሰተ ድረስ -እንዲያወልቅ ወይም እንዲለብስ አይገደድም ፡፡ በባዶ እግሩ ከሆነ በዚያው ይሰግዳል፡፡ በጫማም ከሆነ ከነጫማው ይሰግዳል ፡፡[4]

---

[3] ግዴታ የሆኑ -በቀን አምስት ጊዜ የሚሰገዱት ሰላቶች (ተርጓሚው)፡፡

4 በጫማ መስገድ ከሱና እንደሚቆጠር ግልጽ ሆኖ ሳለ ነገር ግን የመስጂድ ምንጣፎችን በጫማ ማቆሸሽ ግን ተገቢ አይደለም፡፡ ሱዑድ አዘማናን ባዘጋጀው "አል-አህካም አሸርዒያህ ሊነዕል ወልኢንቲዓል" በተባለው መጣጥፍ እንደሰፈረው ሸይኽ አልባኒ እንዲህ ብለዋል "ስለፍይ ወንድሞቼ በዚህ ጉዳይ ላይ-በተነጠፉ መስጂዶች ዉስጥ በጫማ መስገድን በተመለከተ- እንዳያከሩ መክሬያለሁ፡፡ ምክኒያቱም በዘመናችን ባሉት ቆንጆ ምንጣፎች በተነጠፉባቸው መስጅዶችና የነብዩﷺ መስጅድ በመጀመሪያ ዘመኑ በነበረበት ሁኔታ መካከል ልዩነት ስላለ ነው፡፡ ይህንንም ከዚህ ጋር ከሚሄድ ሌላ የሱና ምሳሌ ጋር አቆራኘሁላቸው፡፡ ነብዩﷺ እየሰገደ አኽታ ወይም ምራቅ የመጣበት ሰው ወደ ግራ ወይም ከእግሮቹ ስር እንዲተፋ አዘዋል፡፡ ይህ ግልጽ በሆነ መልኩ የመስጅዱ ወለል አሸዋ ወይም ጠጠር ከሆነ ነው፡፡ ዛሬ ግን የመስጅድ ወለሎች ላይ ምንጣፎች ተዘርግቷል፤ ስለዚህም ምንጣፍ ላይ መትፋት ይቻላል እንደማይሉት በጫማ መስገድም እንዲሁ ነው" ይህንኑ ሀሳብ ከሸይኽ አልባኒ በፊት አል ኢማም አህመድ ብለዉት ነበር፡፡ ኢብኑ ረጀብ የቡኻሪን ሀዲሶች ባብራሩበት መጽሀፋቸው ፈትሁልባሪ እንዲህ ብለዋል "በክር ኢብኑ ሙሀመድ እንዲህ ብለዋል፡ ለኢማም አህመድ እንዲህ አልኳቸው፤ አንድ ሰው መስጅድ ዉስጥ እየሰገደ ቢተፋና በእግሩ መሬት ላይ ቢያሸው ምን ይመስልዎታል? እንዲህም መለሱልኝ፤ የሀዲሱ መልዕክት ይህ ብቻ አይደለም፡፡ አሁን መስጂዶች ዉስጥ ሰሌን ተነጥፎባቸዋል እንደድሮ አይደሉም፡፡" በዘመናችን የኖሩ ታዋቂ ዑለማዎችም ይህንኑ ጥልቅ ማስተዋል ያለበት ምክር ሰጥተዋል፡፡ ለማመሳከር ተከታዮቹን ምንጮች ይመልከቱ፤ የሳዑዲ አረብያ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ (ቅጽ 6/ ገፅ 213-216) / ሸይኽ አብዱልዓዚዝ ኢብኑ ባዝ (ፈታዋ ኑሩን አለደርብ ቅጽ 9 / ገፅ 362 ጥያቄ 164) ሸይኽ ሙሀመድ ቢን ሳሊህ አል-ዑሰይሚን (መጅሙዕ ፈታዋ ቅፅ 12/ 310) (ተርጓሚው)

15. ጫማውን ካወለቀው በቀኝ ጎኑ ማስቀመጥ የለበትም ። በግራ በኩል የሚሰግድ ሰው ከሌለ በግራ ጎኑ፤ ካልሆነም በሁለት እግሮቹ መሀል ያስቀምጠዋል ። ከነብዩ ﷺ የተገኘው ትክክለኛው ተግባር ይህ ነው ።[5]

## የኹጥባ መድረክ(ሚምበር) ላይ መስግድ[6]

16. ለሰላት አሰጋጅ ኢማም ሰዎችን ለማስተማር እንደ ሚንበር ባለ ከፍ ያለ ቦታ መስገድ ይፈቀድለታል። አላሁ አክበር ባማለት በሚንበሩ ላይ ይቆማል፤ እዚያው ሚንበሩ ላይ ይቀራል ሩኩዕም ያደርጋል ። ሱጁድ ማድረግ እንዲችል ወደ ኋላ በመመለስ በሚንበሩ መነሻ መሬት ላይ ሱጁድ ያደርጋል ። የሚቀጥለውንም ረከዓ ወደ ሚንበሩ በመመለስ በተመሳሳይ ሁኔታ ይጨርሳል ።

## ሱትራ አድርጎ መስገድ

17. ከፊት ለፊቱ ሱትራ (ከለላ) አድርጎ መስገድ ግዴታው ነው ። መልዕክተኛው ﷺ በሚከተለው ንግግራቸው እንዲህ ብለዋልና፡-

"لا تصل إلا إلى سترة، ولا تدع أحداً يمر بين يديك ، فإن أبى فلتقاتله فإن معه القرين يعني الشيطان»

*"ከለላ(ሱትራ) አድርገህ ካልሆነ በስተቀር አትስገድ ። ከፊት ለፊትህ (በከለላውና በአንተ መሀል) የሚያልፍን ማንም አካል አታሳልፉ፤ እንቢ ካለ የታገለው ። ሰይጣን ከእርሱ ጋር ተቆራኝቷልና።"*

ይህም ንግግራቸው በጥቅሉ ስለተገለጸ የሚሰግደው በመስጊድ ውስጥም ሆነ ከመስጊድ ውጪ፤ መስጊዱ ትልቅም ሆነ ትንሽ (ከለላ ከማድረግ አንጻር) ልዩነት እንደሌለው ያሳያል ።

18. ነብዩ ﷺ አዘዋልና፤ ወደ ከለላውም መጠጋት ግዴታ(ዋጂብ)[7] ነው።

19. ነብዩ ﷺ ሱጁድ በሚያደርጉበት ቦታ እና በግድግዳው መሀከል ያለው ክፍተት በግ ሊያሳለፍ የሚችል ያህል ብቻ ነበር። ይህን የተገበረ በእርግጥ ግዴታውን ተወጥቷል ።[8]

---

5 ከዚህም በሁሉም እኔ ባየኋቸው የሶሪያ መስጊዶችም ሆነ በሌሎች መስጊዶች ከግርግዳ ወይም ከምሰሶ ርቀው የሚሰግዱ ሰዎች ከመልዕክተኛው ﷺ ትእዛዝና ተግባር መዘናጋታቸው እንጂ ሌላ አለመሆኑን እንረዳለን ።

5 ይህ የነቢዩﷺ ሀዲስ ጫማን ፊት ለፊት ማስቀመጥ እንደማይቻል በግልፅ ያመላክታል ። ነገር ግን ብዙ ሰጋጆች ጫማቸውን ፊት ለፊታቸው በማስቀመጥ ይህን ስርዓት ሲተላለፉ ይታያሉ ።

6 አቡዳዉድ በዘገቡት ሀዲስ አሰጋጅ ኢማም ከሰጋጆች በላይ ከፍ ያለ ቦታ ላይ መስገዱ የተከለከለ ነው። ሆኖም ግን ለማስተማር ከሆነ ሁሉቱንም በመፈጸም ሱጁድ ሲያደርግ ወደመሬት ዝቅ ይላል። (ተርጓሚው)

7 ጸሀፊው በመግቢያው ላይ እንደገለፁት ዋጅብን መተው ልክ ሩክንን እንደመተው ሰላትን አያበላሽም ቢሆንም ካለምንም ምክኒያት ሱትራን የሚተው ሰው ይጠየቅበታል። ይህንን ሸይኹ በፈትዋቸው ገልጸዉታል። የሰላቱን ምንዳም ሊያጎድል ይችላል። (ተርጓሚው)

## የከለሏው ከፍታ ልክ

20. ከለላው ከመሬት አንድ ወይም ሁለት ስንዝር ያህል ከፍ ማለቱ ግዴታ ነው ። የሚከተለውን የመልዕክተኛውን ﷺ ንግግር በመመርኮዝ።

"إذا وضع أحدكم بين يديه مثل مؤخرة الرّحل فليصل، ولا يبالي من وراء ذلك."

*«አንዳችሁ እፊት ለፊቱ የኮርቻ የኋላ መደገፊያ [9] ያህል ከፍታ ያለው ከለላ ካስቀመጠ ይስገድ ። ከከለላው በስተጀርባ ላለው (ለሚያልፍ) አይጨነቅ።»*

21. ከለላውንም ከፊት ለፊቱ ቀጥታ (በግንባሩ አቅጣጫ ) ያደርገዋል። «ወደ ከለላ እንጂ አትስገድ ...» የሚለው ሀዲስ በግልፅ የሚያሳየው ይህንን ነውና ። ከከለላው ቀጥታ ላለመሆን ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ በትንሹም ቢሆን መዘንበል ከመልዕክተኛው ﷺ አልተገኘም።

22. በተተከለ በትር፣ በዛፍ ወይም ምሰሶ፣ አልጋ ላይ ተሸፍና በተኛች ባለቤትህን ሱትራ አድርገህ መስገድ ትችላለህ። በግመልም ቢሆን እንስሳትንም እንደዚሁ ከለላ ማድረግ ይቻላል።

## ወደ ቀብር መስገድ

23. ወደ ቀብር ዞሮ መስገድ በምንም መልኩ አይቻልም። ቀብሩ የነቢያቶችም ይሁን የሌላ።

## ከሰጋጅ ፊት ለፊት ማለፍ ክልክል መሆኑ

24. ከለላ አድርጎ በሚሰግድ ሰው ፊት ለፊት (በከለላውና በሰጋጁ መሀል ) ማለፍ የተከለከለ ነው ። በመስጂደል ሀረምም ሆነ በሌላ መስጊድ ልዩነት የለውም ። የሚከተለው የመልዕክተኛው ﷺ ንግግር ሁሉንም መስጊዶች የሚያካትት በመሆኑ ።

«لو يعلم المار بين يدي المصلي ماذا عليه لكان أن يقف أربعين، خيرا له من أن يمر بين يديه.» يعني المرور بينه وبين موضع سجوده

*«ከሰጋጅ ፊት የሚያልፍ (ሰው) ያለበትን (ወንጀል) ቢያውቅ ኖሮ፣ ከሚያቋርጥ አርባ መቆሙ በተሻለው ነበር።»*[10] ማለትም ከሱ እና ከስጁድ ቦታው መሀል ማለፍ።

---

[8] ከበሶሪያም ሆነ በሌሎች ሀገራት ባየኋቸው መስጊዶች ከግርግዳ ወይም ከምሰሶ ርቀው የሚሰግዱ ሰዎች ከመልዕክተኛው ﷺ ትእዛዝና ተግባር መዘናጋታቸው እንጂ ሌላ አለመሆኑን ከዚህ እንረዳለን።

[9] ሙአኺረቱ ረሀል፦ ይህ በግመል ጀርባ ላይ የሚቀመጠው ኮርቻ መደገፊያ ቋሚ ነው። ይህ ሀዲስ በመሬት ላይ ያለን መስመር (ለከለላነት) መጠቀም እንደማይፈቀድ ያመላክታል። ይህን የሚፈቅደው ሀዲስ ደካማ(ደዒፍ) ነው፣ ለመረጃነት አይበቃም።

[10] መልዕክተኛው ﷺ ጠዋፍ በሚደረግበት ክልል ውስጥ፣ ሰዎች ከፊት ለፊታቸው እየተላለፉ ያለ ከለላ ሰግደዋል የሚለው ሀዲስ ትክክለኛ -ሶሂህ- አይደለም። ሰዎች በሳቸውና በሱጁድ ቦታቸው መሀል መተላለፋቸውንም አይገልፅም ።

### በሰጋጅ ፊት ለፊት ለማለፍ የሚፈልግ አካል እንዳያልፍ መከልከል

*25.* ከለላ አድርጎ የሚሰግድ ሰው፤ ከፊቱ (በከለላውና በሱ መሀል ) ለማለፍ የሚፈልግን ማንኛውንም አካል ማሳለፍ አይገባውም፡፡ *"(እየሰገዳችሁ) ከፊት ለፊታችሁ የሚያልፍ ማንንም አካል አትተዉ… .."* የሚለው ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ሀዲስ እንዲሁም የሚከተለው ሀዲስ (ማንም እንዳያልፍ መከላከል እንደሚያስፈልግ) ያዛሉና፡፡

" إذا صلى أحدكم إلى شيء يستره من الناس، فأراد أحد أن يجتاز بين يديه فليدفع في نحره، وليدرأ ما استطاع، (وفي رواية: فليمنعه مرتين)، فإن أبى فليقاتله فإنما هو شيطان."

*"አንዳችሁ ከሰው ከሚከልለው ነገር ኋላ ቆሞ እየሰገደ ሳለ አንድ ሰው ከፊቱ ለማለፍ ከፈለገ ይተናነቀው ፡፡ ያቅሙንም ያህል ይከላከል፡፡ (በሌላ ዘገባ፡- ሁለት ጊዜ ይከልክለው) እንቢ ካለ እሱ ሰይጣን ነውና ይታገለው፡፡ "*

### በሰጋጅ ፊት ለፊት ለማለፍ የሚፈልግ አካል እንዳያልፍ ለመከልከል ወደፊት መራመድ

26. ህጻናት ወይም እንስሳት ከፊት ለፊቱ እንዳያልፉ ለመከልከል እና ከኋላ እንዲያልፉ ለማድረግ አንድ ወይም ከዚያ በላይ እርምጃዎችን ወደ ፊት መራመድ (በሶላት ውስጥ) ይቻላል፡፡

### ሶላትን የሚቆርጡ

27. ሶላት ሲሰገድ ከለላ ማድረግ በጣም አስፈላጊ የሆነበት ዋነኛው ምክንያቱ ከለላ ባለመደረጉ -ከሰጋጁ ፊት ለፊት በሚያልፉ አካላት- ሰላቱ ሊበላሽ ይችላልና ነው፡፡ ከለላ ያላደረገ ሰው ከፊት ለፊቱ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሴት፤ አህያ፤ ወይም ጥቁር ውሻ ካለፉ ሰላቱ ይቆረጣል (ይበላሻል)[11]፡፡

---

[11] ሙስሊም የዘገቡትን ይህንን ሀዲስ ከአቡ ዘር ያስተላለፈው ሰው "ጥቁር ዉሻ ከቀዩ እና ከቢጫው የተለየው በምንድነው?" ብሎ ጠይቆት ነበር፡፡ እርሱም እንዲህ አለው "የወንድሜ ልጅ ሁይ! የአላህ መልዕክተኛን ልክ እንደጠየከኝ ጠይቂያቸው ነበር 'ጥቁር ዉሻ ሰይጣን ነው' አሉኝ" በማለት መለሰለት፡፡ ጥቁር ዉሻ ሰላት የሚቆርጥበትን ምክኒያት ገልጸዉልናል፡፡ ከላይ ባየነው ሀዲስ ላይም በሚሰግድ ሰው ፊት ለፊት በሀይል ለማለፍ የሚሞክርም ሰይጣን ነው፡፡ ይህ ማለት ግን 'ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሴት እና አህያም አብረው የተገለጹት ሰይጣን ስለሆኑ ነው' ሊያስብል አይችልም፡፡ ምክኒያቱም ሁሉም ሰላትን ይቆርጣሉ እንጂ አንድ አይነት አንድ አይነት ናቸው አልተባለም፡፡ ታዲያ ሴት የወንድን ሰላት የምትቆርጥበት ምክኒያት ምንድነዉ? ከተባለ፤ ብዙ ኡለማዎች 'ሴት በወንድ እና በሚሰግድበት ከለላ መካከል ብታልፍ ልቡን ልትሰርቀዉና ከሰላቱ ልታዘናጋው ስለምትችል ነው' ብለዋል፡፡ በሀዲሱ ላይ ሴትን ከአህያ ወይም ከጥቁር ዉሻ ጋር የሚያመሳስል መልዕክት ፈጽሞ የለም፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በሱረቱል ፈትህ ቁጥር 29 ላይ **"የአላህ መልክተኛﷺ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው"** የሚለው አንቀጽ ነብዩንና ባልደረቦቻቸዉን ወጥ በሆነ መልኩ አንድ ላይ ጠቅሷልና ሁሉም መልዕክተኞች ናቸው የሚል ሀሳብ ቢሰነዝር ትክክል አይሆንም፡፡ ይህንን የተረዳ ሰው አብረዉ ለተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ ተመሳሳይ ናቸው የሚል ድምዳሜ አይሰጥም፡፡ ሀዲሱም ይህ አይነት መልዕክት ፈፅሞ የለዉም፡፡ የምዕመናን እናት ዓኢሻ ይህ ሀዲስ አልደረሳትም ነበርና በሰማችው ጊዜ "ከአህያ እና ከዉሾች ጋር አመሳሰላችሁን በአላህ ይሁንብኝ የአላህ መልዕክተኛ እኔ በእርሳቸዉና በቂብላ መሀል ፊትለፊታቸው አልጋ ላይ ተጋድሜ ይሰግዱ ነበር፡፡" ብላ ነበር፡፡ ዑለማዎች ግን ይህ ግንዛቤዋ ትክክል እንዳልነበር እና ሁለቱ ተያያዥ እንዳልሆኑ ገልፀው በየዘመኑ

## 3.ኒያ[12]

28. ማንኛውም ሰጋጅ ለሚሰግደው ሶላት በልቡ ነጥሎ መነየት (ማሰብ) ግድ ይለዋል ። ለምሳሌ፡- ግዴታ የሆነበትን ዝሁር ወይም አስር ሶላት ወይም ሱናን እንደሚሰግድ በልቡ ለይቶ ማሰብ አለበት ። ይህ የሶላት ቅድመሁኔታ ወይም ማዕዘን ነው ። በንግግር (ድምፅን ከፍ አድርጎ) መነየት ቢድዓ[13] እና ከሱና የሚጋጭ ነው ። ከቀደምት መሪዎች (ዑለሞች) ውስጥ ድምፅን ከፍ አድርጎ ስለ መነየት ያስተማረ ማንም የለም።

## 4.ተክቢረተል ኢህራም

29. ሶላቱን " الله أكبر " - አላሁ ክበር- በማለት ይጀምራል ።

ተክቢረተል ኢህራም ማዕዘን ነው። መልዕክተኛውም ﷺ እንዲህ ብለዋልና።

"مفتاح الصلاة الطهور، وتحريمها التكبير، وتحليلها التسليم"

*«የሶላት መክፈቻ ንጽህና ነው ። የተከለከለ እንዲሆን የሚያደርገው ተክቢራ (ተክቢረተል ኢህራም) ሲሆን የተፈቀደ እንዲሆን የሚያደርገው ሰላምታ ነው ።»*[14]

30. በሁሉም ሶላቶች ላይ ተክቢራ ሲል ድምፁን ከፍ አያደርግም። ኢማም ካልሆነ በስተቀር።
31. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የኢማሙን ተክቢራ ሙዓዚኑ ከፍ አድርጎ ማስተጋባት ይችላል ። ለምሳሌ፡- አሰጋጁ ከታመመ ወይም ከኋላው የሚሰግዱ ሰዎች በጣም ብዙ ሆነው ድምፁ የማይሰማ ከሆነ ።
32. ማዕሙሞች[15] ኢማሙ ተክቢራ አድርጎ ከጨረሰ በኋላ እንጂ ተክቢራ ማድረግ አይችሉም ።
33. እጅን ማንሳትና የአነሳሱ ሁኔታ
34. እጆቹን ከተክቢራው ጋር፣ከተክቢራው በፊት ወይም ከተክቢራው በኋላ ያነሳል ። ሁሉም በሀዲስ ተገኝቷልና።
35. ጣቶቹን ዘርግቶ እጆችን ከፍ ያደርጋቸዋል።

---

አንድን ነገር ያወቁ ሰዎች ባላወቁት ላይ መረጃ እንደሚሆኑ ተናግረዋል። ከሚሰግድ ሰው ፊት መጋደም ወይም መቀመጥ ከማለፍ በተቃራኒው ሰላትን እንደማይቆርጥ አብራርተዋል። (ተርጓሚው)

[12] አንድን ነገር ለመስራት ማሰብና ዉሳኔ ላይ መድረስ

[13] በዲን ላይ ያለ መረጃ የተጨመረ አዲስ መጤ ነገር።

[14] የተከለከለ ማለት፡- አላህ (በሶላት ውስጥ) ክልክል ያደረጋቸው ተግባራት ሲሆን፣ ይህም ማለት አንድ ሰው ልክ አላሁ አክበር ሲል በሶላት ውስጥ ገብቷልና ማንኛውም ከዚያ በፊት ይፈቀድለት ከነበረው ተግባር ይከለከላል (ሀራም ይሆንበታል)። የተፈቀደ ሲልም፡ - ከሰላት ውጪ የተፈቀደን ተግባር ለማለት ሲሆን ሲያሰላምት ሶላቱን ጨርሷልና በሶላት ውስጥ የተከለከለው ነገር መልሶ የተፈቀደ (ሀላል) ይሆንለታል።

[15] አሰጋጁን ተከትለው የሚሰግዱ ሰዎች ።

36. መዳፎቹንም በትከሻው አቅጣጫ ያደርጋቸዋል ። አንዳንዴም እስከ ጆሮው ጫፍ ድረስ ከፍ ያደርጋቸዋል።[16]

## እጆችን ማስቀመጥና የአቀማመጡ ሁኔታ

37. ከተክቢራው በኋላ ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ ያደርጋል ። ይህ የነቢያት (ሰላም እና ሶላት ይውረድባቸው) ሱና ነው። መልዕክተኛውም ﷺ ሰሀቦቹን[17] በዚሁ አዘዋል። እጅን ወደ ታች መልቀቅ አይቻልም።
38. ቀኝ እጁን የግራ እጁ መዳፍ ጀርባ -የመዳፉ መገጣጠሚያ እና ክንዱ- ላይ ያስቀምጠዋል።
39. አንዳንዴም በቀኝ እጁ የግራ እጁን ይጨብጣል።

## እጆችን የማስቀመጫ ቦታ

40. እጆቹን በደረቱ ላይ ያስቀምጣል። ለሴትም ሆነ ለወንድ ልዩነት የለውም።[18]
41. ቀኝ እጅን ወገብ ላይ ማድረግ አይፈቀድም።

## ኹሹዕ[19] እና ወደ መስገጃ ቦታ ማየት

42. ሶላቱን ሲሰግድ በውስጡ አላህን መፍራት(ኹሹዕ ማድረግ) አለበት ። እንደ ስዕል እና ጌጣጌጥ የመሳሰሉ ሃሳብን የሚሰርቁ (ኹሹዕን የሚያሳጡ) ነገሮችን መራቅ ይገባዋል። የሚፈልገው ምግብ ቀርቦ እንዲሁም በሽንት ወይም በአይነምድር እየተጨናነቀ መስገድ የለበትም ።
43. በቆመበት የሱጁድ ቦታውን ይመለከታል።
44. ወደ ግራና ቀኝ አይመለከትም ። (ወደ ተለያየ አቅጣጫ) መመልከት ሰይጣን የሰውን ሶላት የሚሰርቅበት መንገድ ነውና።
45. ዐይኑን ወደ ሰማይ ማንጋጠጥም አይችልም።

---

[16] የጆሮን (የታችኛውን ለስላሳውን ክፍል) በአውራ ጣት መንካት ያስፈልጋል የሚሉት ሰዎች በሀዲስ ድጋፍ የላቸውም። በእኔ አመለካከት ይህ ሰጋጅን ይወሰውሳል።

[17] ባልደረቦቹ- በነብዩ ﷺ ያመኑ ፣ በአይናቸውም እሳቸውን ያዩ እና በዚያው እምነታቸው የሞቱ ።

[18] ከደረት ውጪ ሌላ ቦታ እጅን ማስቀመጥ መሰረት የለውም። መረጃው ደካማ ነው።

[19] ውስጣዊ ፍራቻ

# ዱዓኡል ኢስቲፈታህ[20]

46. ከዚያም ከነብዩ ﷺ ከተገኙ ዱዓዎች ተጠቅሞ አላህን ይለምናል :: የመክፈቻ ዱዓዕ -ዱዓዑል ኢስቲፍታህ- ያደርጋል። ዱዓዎቹም ብዙ ሲሆኑ በጣም የታወቀው፡-

سبحانك اللهم وبحمدك وتبارك اسمك وتعالى جدك ولا إله غيرك

**«ሱብሃነከ አላሁመ ወቢሀምዲከ ወተባረከ ኢስሙከ ወተዓላ ጀዱከ ወላዒላሀ ገይሩከ**

***«አላህ ሆይ! የጠራህ ነህ፤ ምስጋና ተገባህ፤ ስምህ ቁዱስ ነው፤ ልዕልናህ ከፍ አለ፤ ካንተ ሌላ አምላክ የለም።»***

ይህም (ዱዓዕ) የተረጋገጠ የነብዩ ﷺ ትዕዛዝ በመሆኑ በደንብ ሀፍዞ መያዝ ይገባል።

## 5.ቂራአ

47. ከዚያም አላህ (ከሰይጣን) እንዲጠብቀው ይለምናል። ግዴታ ነው። ከተወዉ ይወነጀላል።

48. ሱናው አንዳንዴ፡- "أعوذ بالله من الشيطان الرجيم من همزه ونفخه ونفث" «አዑዙቢላሂ ሚነ ሸይጧኒረጂም ሚን ሀምዚሂ ወነፍኪሂ ወነፈሲሂ።» ማለት ሲሆን

*«ከተረገመው ሰይጣን ከጉትጎታው፣ ከንፋቱ እና ከእስትንፋሱ በአላህ እጠበቃለሁ ።»* እዚህ ላይ (እስትንፋሱ) ሲል፡- ከተጠላው ግጥሙ ለማለት ነው።

49. አንዳንዴ ደግሞ፡ - " ... أعوذ بالله السميع العليم من الشيطان الرجيم" «አዑዙ ቢላህሂ አሰሚዒል አሊም ሚነ ሸይጧኒረጂም ሚን ሀምዚሂ ወነፍኪሂ ወነፈሲሂ።» ማለት ነው።

*«ከተረገመው ሰይጣን ከጉትጎታው፣ ከንፋቱ እና ከእስትንፋሱ ሰሚ እና አዋቂ በሆነው አላህ እጠበቃለሁ ።»*

50. ከዚያም በጀህሪያህም ሆነ በሲሪያ[21] ሶላቶች ላይ ድምፁን ሳያሰማ፡-

***«ቢስሚላሂረህማኒረሂም»*** ይላል። "بسم الله الرحمن الرحيم"

### ፋቲሀን መቅራት

51. ከዚያም ፋቲሃን በሙሉ ይቀራል ። ቢስሚላሂ የፋቲሃ አካል ነው ። ፋቲሃን መቅራት ማዕዘን ነው ። ያለ ፋቲሃ ሶላት ተቀባይነት የለውም ። አረብኛን የማይችል ሰው ፋቲሃን በቃሉ ማጥናት (መሀፈዝ) ግድ ይለዋል።

---

[20] ከተክቢረተል ኢህራም ቀጥሎ የሚደረግ የመግቢያ ዱዓዕ ነው።

[21] ጀህሪያ -ድምፅ ከፍ ተደርጎ ቁርዓን የሚቀራበት የሶላት አይነት አይነት ሲሆን ሲሪያ ደግሞ ድምጽ ዝቅ ተደርጎ ቁርዓን የሚቀራበት የሶላት አይነት ነው።

52. ፋቲሃን መቅራት የማይችል (የሚከተለውን) ማለቱ ያብቃቃዋል።
" سبحان الله والحمد لله ولا إله إلا الله الله أكبر ولا حول ولا قوة إلا بالله "
«ሱብሃነላህ፣ ወል-ሀምዱ ሊላህ፣ ወላ-ኢላሀ ኢለላህ፣ ወላሁ አክበር፣ ወላ-ሀውለ ወላ-ቁወተ ኢላ-ቢላህ።»
*«አላህ ከጉድለቶች ሁሉ ጠራ። ምስጋና ለአላህ ነው። ከአላህ ሌላ ጌታ የለም። አላህ ታላቅ ነው። ብልሀትም ጉልበትም የለም አላህ ዘንድ እንጂ።»*
53. ፋቲሃን -በእያንዳንዱ አንቀጽ መጨረሻ ትንሽ እየተቆመ- አንቀፅ በአንቀጽ መቅራት የተወደደ ነው። ማለትም፡- ( بسم الله الرحمن الرحيم ) ፡ ትንሽ ዝም ይልና፡-
(الحمد لله رب العالمين); ከዚያም ትንሽ ዝም ይልና፡-
(الرحمن الرحيم); ትንሽ ዝም ይልና፡-
( مالك يوم الدين) ከዚያም ትንሽ ዝም ይላል፤ ..... በእንደዚሁ ሁኔታ ይጨርሳል ። የነብዩ ﷺ አቀራር እንዲህ ነበር። በትርጉም ተያያዥነት ያለው አንቀፅ ቢሆንም እንኳ አያከታትሉም ። በያንዳንዱ አንቀፅ መጨረሻ ትንሽ ዝግ ይሉ ነበር።
54. ፋቲሃን ሲቀራ፡- (مالك) ወይም (ملك) ማለትም ማሊኪ ወይም መሊኪ ብሎ መቅራት ይቻላል ።

## የማዕሙም[22] ፋቲሀ አቀራር

55. በሲሪያም ሆነ በጀህሪያ ሶላቶች ላይ ማዕሙም የሆነ ሰው ከኢማሙ ኂላ ፋቲሃን የመቅራት ግዴታ አለበት። በጀህሪያ ሶላት ላይ (አንዳንድ) ኢማሞች የሚቀሩትን ጨርሰው -ማዕሙሞች እንዲቀሩ ግዜ ለመስጠት- ትንሽ ዝም ይላሉ። ይህ ዝምታ በሀዲስ አልተረጋገጠም።[23]

## ከፋተሀ ቀጥሎ ተጨማሪ አንቀፃችን መቅራት

56. በመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዐዎች ላይ ከፋቲሃ በተጨማሪ ሌላ ምዕራፍ ወይም የተወሰኑ አንቀፆችን መቅራት የተወደደ ነው -በጀናዛህ ሶላት ቢሆንም እንኳ።
57. የሚቀራው አንቀፅ አንዳንዴ ያረዝመዋል ። አንዳንዴ ያሳንሰዋል ። በተለይ፡- በጉዞ ላይ፤ በሳል (ጉንፋን) ወይም በህመም ወቅት እና ህፃን ልጅ በሚያለቅስበት ጊዜ የሚቀራው አንቀፅ ብዛት ማነስ አለበት ።
58. የሚቀራው አንቀፅ ብዛት እንደ ሶላቱ አይነትም ይለያያል ። አብዛኛውን ጊዜ የሱብሂ ሶላት በጣም ረጅም ሲሆን ከዚያም ዙሁር፣ አስር፣ ኢሻዕ፣ በመጨረሻም መግሪብ በቅደም ተከተል እያጠረ ይመጣል ።
59. ከሁሉም ሰላቶች የሌሊት ሶላት ይበልጥ ረጅም ነው ።

---

[22] አሰጋጁን ተከትሎ የሚሰግድ ሰጋጅ።
[23] ይህን (ዝምታ) የሚደግፉ ሰዎች የሚጠቀሙት መረጃ ትክክለኛ አለመሆኑን በ"ሲልሲለቱል አህዲሱ ደኢፍህ" በሚለው መፅሀፍ ገልጫለሁ።

60. (በየትኛውም ሶላት ላይ) የመጀመሪያውን ረከዓ ከሁለተኛው ረከዓ ይበልጥ ማርዘም ሱና ነው ፡፡
61. በመጨረሻዎቹ ሁለት ረከዓዎች ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዓዎች አንጻር በግማሽ ያህል የሚያንስ አንቀፆችን መቅራት ሱና ነው ፡፡[24]

## በያንዳንዱ ረከዐ ላይ ፋቲሀን መቅራት

62. በያንዳንዱ ረከዓ ላይ ፋቲሃን መቅራት ግዴታ ነው ፡፡
63. አንዳንድ ጊዜ በመጨረሻዎቹ ሁለት ረከዓዎች ላይ ከፋቲሃ በተጨማሪ የተወሰኑ የቁርዓን አንቀፆችን መቅራት ሱና ነው፡፡
64. ኢማም ለሆነ ሰው በሃዲስ ከመጣው በላይ ብዙ አንቀጾችን መቅራት አይፈቀድለትም ፡፡ ከተከታዮች ውስጥ በእድሜ የገፉ ሽማግሌ፣ በሽተኛ፤ አጥቢ እናት ወይም የሚቸኩል ሰው ሊኖሩ እና በመርዘሙም ሊቸገሩ ይችላሉና፡፡

## ድምፁን አሰምቶ ወይም ሳያሰሙ መቅራት

65. በሱብሂ፣ በጁምዓ፣ በዒድ፣ በሶላቱል ኢስቲስቃዕ [25] ፣ በሶላቱል ኹሱፍ [26] ፣ እና በመግሪብና ኢሻዕ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዓዎች ላይ ድምፁን በማሰማት ይቀራል ፡፡ በዙሁር፣ በአስር፣ በመግሪብ በሶስተኛው ረከዓ፣ እና በኢሻዕ በመጨረሻዎቹ ሁለት ረከዐዎች ላይ ደግሞ ድምፁን ሳያሰማ ይቀራል ፡፡
66. በሲሪያ ሶላቶች ውስጥ ኢማም አንዳንዴ የተወሰኑ አንቀፆችን ማሰማት ይችላል
67. በሌሊት ሶላትና ዊትር ላይ አንዳንዴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሌላ ጊዜ ደግሞ ድምፁን ዝቅ አድርጎ ቁርዓንን ይቀራል፡፡ ድምፁን ከፍ ሲያደርግ በመካከለኛ ድምፅ መሆን አለበት ፡፡

## ቁርአንን አስውቦ መቅራት

68. ትርጉሙን አንድ በአንድ በማስተንተን በጣም ሳይፈጥን በጣምም ዝግ ሳይል ድምጹን በማሳመር መቅራቱ ሱና ነው ፡፡ በቢድዓ (ፈጠራ) ባልተቤቶች ወይም በሙዚቀኞች ዜማ መሰረት ሳይሆን የታወቀውን[27]ስርዓትን በመከተል ድምፁን ያዜማል ፡፡

## ኢማም ሲሳሳት ማስተካከል

69. ኢማም ቁርዓን ሲቀራ ከተሳሳተ ተከታዮች ማረም ይገባቸዋል ፡፡

---

[24] የዚህን ማብራሪያ ከፈለግክ በ "ሲፈቲ ሰላት..." መጽሀፍ (አረብኛ) ገፅ 102 ተመልከት ፡፡
[25] ዝናብ ሲጠፋ የሚሰገድ ሶላት፡፡
[26] ፀሃይ ወይም ጨረቃ ሲጋረድ የሚሰገድ ሶላት ፡፡
[27] በሩኩዕ ላይ የሚባሉ ሌሎች ውዳሴዎች አሉ ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡- አጫጭር፣ መካከለኛና ረጃጅም ውዳሴዎች ይገኙበታል ፡፡ «ሲፋቲ ሶላት... » (አረብኛ) ገፅ 132 ተመልከት፡፡

# 6. ሩኩዕ

70. ሰጋጁ የሚቀራውን እንደጨረሰ ትንፋሹ እስኪረጋጋ ድረስ ለትንሽ ጊዜ በዝምታ ይቆማል ::
71. ከዚያም በተክቢረተል ኢህራም ላይ ባሳለፍነው አኳኋን እጁን ከፍ ያደርጋል ::
72. አላሁ አክበር ይላል:: ግዴታ ነው::
73. ሁሉም አካሎች ቦታቸውን እስኪይዙና መገጣጠሚያዎቹ እስኪረጉ ድረስ ሩኩዕ ያደርጋል :: ማዕዘን ነው::

## የሩኩዕ አደራረግ

74. እጁን ጉልበቱ ላይ በማድረግ፤ በጉልበቱ ላይ ማመቻቸት፤ በጣቶች መሀል ክፍተትን በመፍጠር ጉልበትን መጨበጥ:: ግዴታዎች ናቸው::
75. ውሃ ወገቡ ላይ ቢጨመር አይፈስም በሚያስብል ያክል ወገቡን አስተካክሎ ቀጥ ያደርጋል :: ይህም ግዴታ ነው::
76. ጭንቅላቱን ቀና ሳያደርግ ወይም ሳያቀረቅር ቀጥ አድርጎ ከወገቡ ጋር ያስተካክለዋል ::
77. ክርኖችን ከጎኑ ያርቃቸዋል ::
78. ሶስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ፡ - " سبحان ربي العظيم " «ሱብሃነ ረቢየል አዚም ::» *«ሀያሉ ጌታ ጥራት ተገባው::»* ይላል::[28]

# የእያንዳንዱ ማዕዘን ቆይታ ማቀራረብ

79. የእያንዳንዱን ማዕዘን ቆይታ (ርዝመት) እኩል ወይም የተቀራረበ ማድረግ ሱና ነው :: ይህም ማለት፡- ቂያምን፣ ሩኩዕን፣ ኢዕቲዳልን [29] ፣ ሱጁድን፣ እና ጁሉስን [30] የተቀራረበ ቆይታ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው::
80. በሱጁድ እና በሩኩዕ ላይ ቁርዓን መቅራት አይቻልም ::

# ከሩኩዕ መነሳት (ኢዕቲዳል)

81. ከዚያም ወገቡን ከሩኩዕ ያነሳል :: ማዕዘን ነው::
82. ከሩኩዕ ሲነሳ፡- سمع الله لمن حمد «ሰሚአላሁ ሊመን ሀሚደህ» ይላል:: ግዴታ ነው::

---

[28] በሩኩዕ ላይ የሚባሉ ሌሎች ውዳሴዎች አሉ:: ከነዚህም ውስጥ፡- አጫጭር፣ መካከለኛና ረጃጅም ውዳሴዎች ተካተውበታል:: «ሲፋቱ ሶላት… » (አረብኛ) ገፅ 132 ተመልከት::
[29] ከሩኩዕ በኋላ መቆም
[30] በሁለቱ ሱጁዶች መሀል መቀመጥ

*«አላህ የአመሰጋኙን ምስጋና ተቀባይና ሰሚ ነው።»*

83. ከሩኩዕ ሲነሳ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን እጁን ከፍ ያደርጋል።
84. ከዚያም ሁሉም አጥንቶቹ ቦታቸውን እስኪይዙ ድረስ ቀጥ ብሎና ተረጋግቶ ይቆማል። ማዕዘን ነው።
85. ከቆመ በኋላ፡- " ربنا ولك الحمد " «ረበና ወለከል ሀምድ »ይላል።[31]

*«ጌታችን ሆይ ምስጋና ላንተ የተገባ ነው።»*

*ይህንንም ማለት በሁሉም ሰጋጆች ላይ ግዴታ ነው። ኢማምም እንኳ ቢሆን።*[32]

*«ሰሚአላሁ ሊመን ሀሚደህ»* ሲቆም የሚባል ውዳሴ ሲሆን *«ረበና ወለከል ሀምድ»* ከተቆመ በኋላ የሚባል ውዳሴ ነው።[33]

86. ከፍ ብሎ እንደተገለፀው የዚህን ቂያም እና የሩኩዕን ቆይታ እኩል ያደርጋል።

# 7. ሱጁድ

87. ከዚያም፡- " الله أكبر " ይላል። ግዴታ ነው።
88. አንዳንዴም እጁን ያነሳል።

## እጅን አስቅድሞ ወደ ሱጁድ መውረድ

89. ከጉልበት በፊት እጁን በማስቀደም ወደ ሱጁድ ይወርዳል። መልዕክተኛው ﷺ ከግመል መንበርከክ ጋር መመሳሰልን በመከልከል እጅን በማስቀደም ወደ ሱጁድ መውረድን አዘዋል። ከተግባራቸው የተገኘውም ይኸው ነው። ግመል በፊት ለፊት እግሮቿ ላይ በሚገኘው ጉልበቷ ነው የምትንበረከከው።[34]
90. መዳፎቹን በመደገፍ ሱጁድ ያደርጋል። ይዘረጋቸዋልም። ማዕዘን ነው።
91. የእጅ ጣቶቹን ያጠጋጋል።
92. ወደ ቂብላም ያቅጣጫቸዋል።
93. የእጅ መዳፎቹን በትከሻው ትይዩ ያደርጋቸዋል።
94. አንዳንዴ (መዳፎቹን) በጆሮው አቅጣጫ ያደርጋል።

---

[31] ሌሎች ውዳሴዎችም አሉ። «ሲፈቲ ሰላት… » የሚለውን (የአረብኛ) መፅሀፍ ይመልከቱ።

32 (ከሩኩዕ በኋላ) ሲቆም እጅን ደረት ላይ ማድረግ ከመልዕክተኛው ﷺ አልተገኘም። ሰፊ ትንታኔ ከፈለግክ «ሲፋቲ ሰላት…» የሚለውን መፅሐፌን ተመልከት።

[33] ከሩኩዕ በኋላ እጅን ደረት ላይ መመለስ ይቻላል ወይስ አይቻልም ? በሚለው ጉዳይ ላይ ምሁራን ተወዛግበዋል። የዚህ መፅሐፍ ፀሐፊ አይቻልም ከሚሉት ውስጥ ናቸው። (ተርጓሚው)

[34] ሱጁድ ሲወረድ እጅ ወይስ ጉልበት መቅደም አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ በምሁራን መሀል ልዩነት አለ። (ተርጓሚው)

95. ሁለት ክንዶቹን ከመሬት ከፍ ያደርጋል ። ይህም ግዴታ ነው ። እንደውሻ ክንድን መሬት ላይ መዘርጋት አይቻልም።
96. አፍንጫውንና ግንባሩን በመሬት ላይ አስተካክሎ ያስቀምጣል ። ማዕዘን ነው።
97. ጉልበቶቹን በመሬት ላይ ያመቻቻል ።
98. የእግር ጣቶቹን ጫፍም እንዲሁ በመሬት ላይ ያመቻቻል ።
99. እግሮቹን በመሬት ላይ ይተክላል። ይህ ሁሉ ግዴታ ነው።
100. የእግር ጣቶቹን ጫፍ ወደ ቂብላ ያዞራል።
101. ተረከዞቹን ያቀራርባል።

### ተስተካክሎ ሱጁድ ማድረግ

102. ስጁድ ሲያደርግ አካሎቹን ማስተካከል (አለማወላገድ) ግዴታ ነው ። ይህም የሚሆነው በሁሉም ሱጁድ ማድረጊያ አካላቱ በእኩል መሬት ላይ ሲያርፍ ነው ። እነሱም፡-ግንባር አፍንጫን ጨምሮ፣ ሁለት የእጅ መዳፎች፣ ሁለት ጉልበቶች፣ የሁለቱ እግር ጣቶች ናቸው ።
103. በእንደዚህ ሁኔታ በሱጁድ ላይ የተስተካከለ በእርግጥ እርጋታን አግኝቷል ። በሱጁድ ላይ መርጋት (ኢጥሚዕናን) ከማዕዘኖች ነው።
104. በሱጁዱ ላይም ሶስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ፡- "سبحان ربي الأعلى" «ሱብሃነ ረቢየል አዕላ» ይላል።[35]

*«የበላይ የሆነው ጌታዬ ጥራት ይገባው።»*

105. በሱጁድ ላይ የሚደረግ ዱዓ ይበልጥ ተቀባይነት ይኖረዋል ተብሎ ስለሚገመት በሱጁድ ላይ ዱዓ ማብዛቱ የተወደደ ነው።
106. ከፍ ብሎ እንደተገለፀው፤ የሱጁዱን ቆይታ ከሩኩዕ ቆይታ ጋር የተቀራረበ እንዲሆን ያደርገዋል ።
107. (በባዶ) መሬት ወይም ልብስን፣ ምንጣፍን፣ ሰሌንን አሊያም ሌላ ተመሳሳይ ነገርን አንጥፎ ሱጁድ ማድረግ ይቻላል።
108. በሱጁድ ላይ ሆኖ ቁርዓን መቅራት አይችልም ።

# 8. በሱጁዶች መሀል ኢፍቲራሽ[36] እና ኢቅዓእ[37]

109. ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ጭንቅላቱን ከሱጁድ ያነሳል ። ግዴታ ነው።
110. አንዳንዴም እጁን -ከተክቢራው ጋር- ያነሳል።

---

[35] ሌሎች በሱጁድ ላይ የሚባሉ ውዳሴዎችም አሉ ።
[36] ቀኝ እግርን ተክሎ በግራ እግር ላይ መቀመጥ ።
[37] ሁለቱ እግሮችን አቁሞ በተረከዞች ላይ መቀመጥ ።

111. ሁሉም አጥንቶቹ ቦታቸው እስኪመለሱ ድረስ ተረጋግቶ ይቀመጣል ። ማዕዘን ነው።
112. ግራ እግሩን በማስተኛት በላዩ ይቀመጣል ። ግዴታ ነው።
113. ቀኝ እግሩን በመሬት ላይ ይተክላል ።
114. የቀኝ እግር ጣቶቹን በማጠፍ ወደ ቂብላ ያቅጣጫል ።
115. አንዳንዴም ሁለት እግሮቹን በመሬት ላይ በመትከል በተረከዙ ላይ ይቀመጣል ።
116. ከተቀመጠም በኋላ፡-

" اللهم اغفر لي، وارحمني، واجبرني، وارفعني، وعافني، وارزقني. "

«አላሁመ ኢግፊርሊ፣ ወርሀምኒ፣ ወጅቡርኒ.፣ወርፊዕኒ፤ወዓፊኒ ፣ወርዙቅኒ።» ይላል።
*«አላህ ሆይ! ማረኝ፣ እዘንልኝ፣ ጠግነኝ፤ ደረጃይንም ከፍ አድርግልኝ፣ ወንጀሌንም እለፍልኝ፣ ሲሳይንም ስጠኝ።»*

117. ከፈለገም፡- "رب اغفر لي، رب اغفر لي" «ረቢግፊርሊ፣ ረቢግፊርሊ ። »ይላል።
«ጌታይ ሆይ ምህረትህን ለግሰኝ፣ጌታይ ሆይ ምህረትህን ለግሰኝ ።»
118. ይህን አቀማመጥ ከሱጆዱ ጋር የተቀራረበ ቆይታ እስኪኖረው ድረስ ያዘገየዋል ።

## ሁለተኛው ሱጁድ

119. ከዚያም፡- አላሁ አክበር ይላል። ግዴታ ነው።
120. አንዳንዴም ከዚህ ተክቢራ ጋር እጁን ያነሳል ።
121. ሁለተኛውን ሱጁድ ያደርጋል። ማዕዘን ነው።
122. በመጀመሪያው ሱጁድ ላይ ያደረገውን በዚህኛውም ሱጁድ ላይ ይደግማል ።

## ጀልሰተል ኢስቲራሀ[38]

123. ሁለተኛውን ረከዓ ለመስገድ ከስጁድ ሲነሳ አላሁ አክበር ይላል ። ግዴታ ነው።
124. አንዳንዴም እጁን (ከተክቢራው ጋር) ያነሳል።
125. ወደ ሁለተኛው ረከዓ ከመነሳቱ በፊት ቀና ብሎ ሁሉም አጥንቶቹ ወደ ቦታቸው እስኪመለሱ ድረስ በግራ እግሩ ላይ ተስተካክሎ ይቀመጣል ።

[38] የእረፍት መውሰጃ አቀማመጥ- ከመጀመሪያው ረከዓ ወደ ሁለተኛው ረከዓ ከመነሳት በፊት ትንሽ ጊዜ መቀመጥ ነው።

## 9. ሁለተኛ ረከዓ

126. ከዚያም ጣቶቹን -ለቡኮ እንደሚጨበጠው አይነት - ጨብጦ መሬትን በመመርኮዝ ለሁለተኛው ረከዓ ይነሳል። ማዕዘን ነው።
127. በሁለተኛውም ረከዓ በመጀመሪያው ረከዓ ላይ የፈጸመውን በድጋሚ ይተገብራል፡
128. ዱዓዑል ኢስቲፍታህ ግን አያደርግም።
129. ቆይታውንም (የረከዓውን ርዝመት) ከመጀመሪያው ረከዓ አንጻር ያነሰ ያደርገዋል።

## 10. ለተሸሁድ መቀመጥ

130. ሁለተኛውን ረከዓ ከጨረሰ በኋላ ለተሸሁድ ይቀመጣል። ግዴታ ነው።
131. ቀደም ብሎ (በሁለቱ ሱጁዶች መሀል ሲቀመጥ ) እንደተገለፀው ቀኝ እግሩን በመትከል ግራውን አስተኝቶ በላዩ ላይ ይቀመጣል።
132. ነገር ግን እዚህ ጋ በተረከዘ ላይ መቀመጥ (ኢቅዓዕ) አይቻልም።
133. ቀኝ መዳፉን በቀኝ ጭኑ እና ጉልበቱ ላይ ያደርገዋል። የቀኝ እጁን ክርን ከጭኑ አያርቀውም።
134. ግራ መዳፉንም በግራ ጭኑ እና ጉልበቱ ላይ ይዘረጋዋል።
135. በእጁ (በተለይ በግራ እጁ) መሬትን ተደግፎ መቀመጥ አይችልም።

## ጣትን ማንቀሳቀስ እና ጣቱንም መመልከት

136. የቀኝ እጅ ጣቶቹን ሁሉ ይጨብጣል፤ አንዳንዴ አውራ ጣቱን በመሀል ጣቱ ላይ ያደርጋል።
137. ሌላ ግዜ ደግሞ በአውራጣቱ እና በመሀል ጣቱ እንደ ክብ ያለ ቅርፅ ይሰራል።
138. በአመልካች ጣቱ ወደ ቂብላ ያመላክታል።
139. አይኖቹን (በአመልካች) ጣቱ ላይ ያሳርፋል።
140. ተሸሁድን ጀምሮ እስከሚጨርስ ድረስ የአመልካች ጣቱን ያንቀሳቅሳል።
141. በግራ እጅ ጣቱ ማመላከት አይችልም።
142. ከላይ የተገለፁትን ሁሉ በያንዳንዱ ተሸሁድ ላይ ይፈጽማል።

## የተሸሁድ ይዘቱ እና ከተሸሁድ በኋላ ዱዓዕ ማድረግ

143. ተሸሁድ ማድረግ ግዴታ ነው። ረስቶ ካላደረገም ማካካሻ ሁለት ሱጁድ (ሱጁዱ ሰህው) ያደርጋል።
144. (ተሸሁድን) ድምፁንም ሳያሰማ ያነባል።
145. ይዘቱም እንደሚከተለው ነው።

«التحيات لله، والصلوات، والطيبات، السلام على النبي ورحمة الله وبركاته، السلام علينا وعلى عباد الله الصالحين، أشهد أن لا إله إلا الله، وأشهد أن محمد عبده ورسوله»

*«አተህያቱ ሊላሂ ወሰለዋቱ ወጠይባቱ አሰላሙ አለነቢዩ [39] ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ አሰላሙ አለይና ወአላ ኢባዲላሂ አሷሊሂን አሽሀዱ አንላ-ኢሏሀ ኢለሏሀ ወአሽሀዱ አነ ሙሃመደን አብዱሁ ረሱሉላህ።[40]»*

*«ክብር እዝነቶች እና መልካም ነገሮች ሁሉ የአላህ ናቸው ። የአላህ ሰላም እዝነቱና በረከቶቹ በነብዩ ላይ ይሁን። ሰላም በኛና በደጋጎች የአላህ አገልጋዮች ላይ ይውረድ ። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። ሙሀመድም የአላህ መልዕክተኛ እና አገልጋይ መሆናቸውን እመሰክራለሁ ።»*

146. ከዚያም በኋላ በነብዩ ﷺ ላይ ሰለዋትን ያወርዳል። ይህም፡-

" اللهم صل على محمد، وعلى آل محمد، كما صليت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم، إنك حميد مجيد. اللهم بارك على محمد، وعلى آل محمد، كما باركت على إبراهيم، وعلى آل إبراهيم، إنك حميد مجيد."

«አላሁመ ሰሊ አላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ከማሰለይተ አላ ኢብራሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሀሚዱን መጂድ። አላሁመ ባሪክ ኣላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ከማ ባረክተ አላ ኢብራሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሀሚዱን መጂድ ።»

*«አላህ ሆይ! እዝነትህን ለኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸው እንዳወረድክላቸው ሁሉ ለሙሀመድና ለቤተሰቦቻቸው አውርድላቸው። ለኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸው ረድዔትን እንዳወረድክላቸው ሁሉ ለሙሃመድና እና ለቤተሰቦቻቸው ረድዔት አውርድላቸው። አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና።»*

147. ከተፈለገም በአጭሩ፡-

«اللهم صل على محمد، وعلى آل محمد، وبارك على محمد، وعلى آل محمد، كما صليت وباركت على إبراهيم، وعلى آل إبراهيم، إنك حميد مجيد»

«አላሁመ ሰሊ አላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ወባሪክ ኣላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ከማሰለይተ ወባረክተ አላ ኢብራሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሀሚዱን መጂድ»

*«አላህ ሆይ! እዝነትህንና ረድዔትህን ለኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸው እንዳወረድክላቸው ሁሉ ለሙሀመድና ለቤተሰቦቻቸው አውርድላቸው። አንተ ምስጉኑና ሀያሉ ነህና።»*

148. ከዚያም በሀዲስ ከተገኙት ዱዓዎች የፈለገውን በመምረጥ አላህን ይለምናል ።

---

[39] ይህ መልዕክተኛው ﷺ ከሞቱ በኋላ የተደነገገ ነው። በኢብኑ መስዑድ፣ ዓኢሻ፣ ኢብን ዙበይር እና ኢብን አባስ ተሽሁድ ውሰጥ እንደሚገኝ ተረጋግጠዋል። በዚህ ዙሪያ ማብራሪያ የፈለገ «ሲፈቲ ሰላት... » መጽሀፍ (አረብኛ) ገፅ 161 ይመልከት።

[40] በዚሁ በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ ሌላ አይነት ተሽሁድ ተገልጧል። ይህኛው የተሻለው ነው።

## 11. ሦስተኛ እና አራተኛ ረከዓ

149. ከዚያም፡- አላሁ አክበር ይላል። ግዴታ ነው። ተቀምጦ ቢል የተወደደ ነው።
150. አንዳንዴ እጁን (ከተክቢራው ጋር) ያነሳል።
151. በመቀጠል ወደ ሶስተኛው ረከዓ ይነሳል። ሶስተኛውም ሆነ አራተኛው ረከዓ ማዕዘን ናቸው።
152. አራት ረከዓ የሚሰግድም ከሆነ በተመሳሳይ ሁኔታ ይተገብረዋል ።
153. ነገር ግን ወደ አራተኛ ረከዓ ከመነሳቱ በፊት ቀና ብሎ ግራ እግሩ ላይ ሁሉም አጥንት ወደ ቦታቸው እስኪመለሱ ድረስ (ለተንሽ ጊዜ) ተስተካክሎ ይቀመጣል።
154. ከዚያም ወደ ሁለተኛው ረከዓ ሲቆም እንዳደረገው መሬትን በእጁ ተመርኩዞ ይቆማል ።
155. በሶስተኛውም ሆነ በአራተኛው ረከዓ ላይ ፋቲሃን ይቀራል። ግዴታ ነው።
156. አንዳንዴ ተጨማሪ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የቁርዓን አንቀፆችን ይቀራል ።

## 12. የአደጋ ጊዜ ቁኑት (አል-ቁኑቱ ሊናዚል)

157. በሙስሊሞች ላይ አደጋ ከመጣ በሶላት ውስጥ ዱዓ (ቁኑት) ማድረግ ሱና ነው።
158. ዱዓው የሚደረገውም ከሩኩዕ ቀጥሎ "ربنا ولك الحمد" ረበና ወለከል ሀምድ ከተባለ በኋላ ነው።
159. በዚህን ጊዜ መደረግ ያለበት የተወሰነ ዱዓ የለም ። ከአደጋው አይነት ጋር የሚስማማ ዱዓ ያደርጋል።
160. እጁን ከፍ አድርጎ ዱዓውን ያደርጋል።
161. ኢማም ከሆነ ድምጹን ከፍ አድርጎ ይለምናል ።
162. ማዕሙሞች አሚን ይላሉ።
163. ዱዓውን ሲጨርስ አላሁ አከበር ብሎ ስጁድ ይወርዳል።

## 13. የዊትር ቁኑት ቦታዉና ይዘቱ

164. የዊትርን ቁኑት አንዳንዴ እንዲደረግ ተደንግጓል ።
165. ቦታውም፡- በአደጋ ጊዜ ከሚደረገው ቁኑት በተለየ ሁኔታ ከሩኩዕ በፊት ነው ።
166. በቁኑቱ ላይ የሚከተለውን ዱዓ ያደርጋል፡-

«اللهم اهدني فيمن هديت، وعافني فيمن عافيت، وتولني فيمن توليت، وبارك لي فيما أعطيت، وقني شر ما قضيت، فإنك تقضي ولا يقضى عليك، وإنه لا يذل من واليت، ولا يعز من عاديت، تباركت ربنا وتعاليت، ولا منجا منك إلا إليك»

«አላሁመ ኢህዲኒ ፊመን ሀደይት፣ ወዓፊኒ ፊመን ዓፈይት፣ ወተወለኒ ፊመን ተወለይት፣ ወባሪክ ሊ ፊማ አዕጠይት፣ ፈኢነከ ተቅዲ ወላዩቅዳ አለይከ፣ ወኢነሁ ላየዚሉ መን ዋለይት፣ ወላ የኢዙ መን ኣደይት፣ ተባረክተ ረበና ወተኣለይት፣ ወላ መንጃ ሚንከ ኢላ ኢለይከ ።»

*«አላህ ሆይ! ሌሎችን ቀናውን መንገድ እንደመራሀው ሁሉ እኔንም ምራኝ፣ ሌሎችን ይቅርታህን እንደ ቸርክ ሁሉ እኔንም ይቅር በለኝ፣ በለገስከኝ ነገር ሁሉ ረድዔትህ አውርድልኝ፣ ከወሰንከው ክፉ ነገር ጠብቀኝ።አንተ ወሳኝ ነህ በአንተ ላይ የሚወስን የለም። አንተ ዋቢ የሆንከው ሰው አይዋረድም። አንተ ጠላት ያደረከው ደግሞ ከፍ ያለ ደረጃ አያገኝም ። ጌታይ ሆይ ረድዔተ ብዙና የላቅክ ነህ ። ከአንተ ዘንድ መሸሻ የለም ወደ አንተ ቢሆን እንጂ።»*

167. ይህ ዱዓዕ ከመልዕክተኛው ﷺ አስተምህሮት ውስጥ ነው። ባልደረቦቹ ይተገብሩት እንደነበረው በ ነብዩ ﷺ ላይ ሰለዋትን ከማውረድ ውጪ በዚህ ዱዓዕ (ቁኑት) ላይ ምንም አይነት ተጨማሪ ዱዓዎችን መጠቀም አይቻልም።[41]
168. ከዚያም ባሳለፍነው ሁኔታ ሩኩዕ አድረጎ ሁለቱን ሱጁዶች ያደርጋል።

## 14. የመጨረሻው ተሸሁድና እና ተወሩክ[42]

169. ከዚያም ለመጨረሻው ተሸሁድ ይቀመጣል። ሁለቱም ግዴታ ናቸው።
170. በመጀመሪያው ተሸሁድ ላይ እንዳደረገው በዚህኛውም ያደርጋል።
171. ነገር ግን በዚህኛው ተሸሁድ ላይ የግራ መቀመጫውን መሬት ላይ በማስደገፍ፣ ተረከዞቹን ወደ ቀኝ ጎኑ በማድረግ፣ የግራ እግሩን በቀኝ ባቱ ስር በማድረግ (በተወሩክ) ይቀመጣል።
172. የቀኝ ተረከዙን በመሬት ላይ ይተክላል።
173. አንዳንዴም (የቀኝ ተረከዙን) ያስተኛዋል።
174. የግራ መዳፉን በግራ ጉልበቱ ላይ ተጭኖ ይደገፈዋል።

## በነብዩ ﷺ ላይ ሰለዋት ማውረድ እና ከአራት ነገሮች አላህን ጥበቃ መለመን

175. በመጨረሻው ተሸሁድ በነብዩ ﷺ ላይ ሰለዋት ማውረድ ግዴታ ነው። ይዘቱን በመጀመሪያው ተሸሁድ ላይ ገልጸናል።

---

[41] በቁኑት ላይ ተጨማሪ ዱዓዎችን መለመን ይቻላል ወይስ አይቻልም? ሌላው ምሁሮች የተለያዩበት ጉዳይ ነው። የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ መጨመር አይቻልም ከሚሉት ጎራ ናቸው። (ተርጓሚው)

[42] ቀኝ እግርን ተክሎ ግራ እግርን በቀኝ እግር ስር በማሾለክ በግራ መቀመጫ መቀመጥ ።

176. ከአራት ነገሮች አላህ እንዲጠብቀው ይለምናል ።

«اللهم إني أعوذ بك من عذاب جهنم، ومن عذاب القبر، ومن فتنة المحيا والممات، ومن شر فتنة المسيح الدجال»

«አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን አዛቢ ጀሀነም፤ ወሚን አዛቢል ቀብሪ፤ ወሚን ፊትነቲል ማህያ ወመማት፤ ወሚን ሸሪ ፊትነቲል መሲሂ ደጃል።» በማለት።

*«ጌታዬ ሆይ! ከጀሀነም እሳት፤ ከቀብር ቅጣት፤ ከህይወትና ከሞት ፈተና እና ከመሲሂ ደጃል ፈተና ባአንተ እጠበቃለሁ።»* [43]

## ከሰላምታ በፊት ዱዓዕ ማድረግ

177. ከዚያም የፈለገውን ዱዓዕ ለራሱ ይለምናል ። ከመልዕክተኛው ﷺ የተገኙ ብዙ ያማሩ ዱዓዎች አሉ ። ከነዚህ ዱዓዎች ጥቂቱን እንኳ የማያውቅ ከሆነ፤ ለመንፈሳዊውም ሆነ ለአለማዊው ህይወቱ ከሚጠቅመው ጉዳይ የተገራለትን ያህል ይለምን ።

## 15. ሰላሙታና አይነቶቹ

178. ከዚያም የቀኝ ጎን ጉንጩ በጣም እስኪታይ ድረስ ወደ ቀኝ በመዞር ያሰላምታል ። ማዕዘን ነው።

179. ወደ ግራም እንዲሁ የግራ ጎን ጉንጩ በጣም እስኪታይ ድረስ በመዞር ያሰላምታል -በሶላተል ጀኢዛህ ቢሆንም እንኳ።

180. በሶላተል ጀናዛህ በስተቀር በሁሉም ሰላቶች ላይ ኢማሙ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያሰላምታል ።

181. የሰላምታ አይነቶች፡-

አንደኛው፡- "السلام عليكم ورحمة الله وبركاته"

«አሰላሙ አለይኩም፣ ወረህመቱላሂ፣ ወበረካቱህ።» - ወደ ቀኝ

*«የአላህ ሰላም፣ እዝነቱ እና በረከቱ በናንተ ላይ ይሁን።»*

"السلام عليكم ورحمة الله" «አሰላሙ አለይኩም፣ ወረህመቱላሂ።» - ወደ ግራ

*«የአላህ ሰላም እና እዝነቱ በናንተ ላይ ይሁን።»*

ሁለተኛ፡- ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ፡- "وبركاته" «ወበረካቱህ» የሚለው ሀረግ (ብቻ) ይቀነሳል።

---

[43] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

ሶስተኛ፡- "السلام عليكم ورحمة الله" «አሰላሙ አለይኩም፣ ወረህመቱላህ።» - ወደ ቀኝ
"السلام عليكم" «አሰላሙ አለይኩም።» -ወደ ግራ
*«የአላህ ሰላም በናንተ ላይ ይሁን።»*

አራተኛ፡- ወደ ፊት ለፊት ዙሮ ትንሽ ወደ ቀኝ እየተዘነበለ፤ አንድ ግዜ፡-
"السلام عليكم" «አሰላሙ አለይኩም» ይላል።

ሙስሊም ወንድሜ ሆይ! ይህ የነቢዩን ﷺ የሶላት አሰጋገድ ላንተ ግልፅ፤ በአዕምሮህ ለመሳል እንዲመችህ እና በአይንህ ፍንትው ብላ እንደትታይህ ለማድረግ በማሰብ እጥር ምጥን አድርጌ ያቀረብኩት ጽሑፍ ነው። የነቢዩን ﷺ የሶላት አሰጋገድ በገለፅኩት ሁኔታ ከሰገድክ አላህ ሶላትህን እንደሚቀበልህ ተስፋ አደርጋለሁ ። ምክንያቱም ይህን በመፈፀምህ በእርግጥ «አሰጋገዱን አይታችሁ ስገዱ ።» የሚለውን የመልዕክተኛውን ﷺ ትዕዛዝ በተግባር ማሳየት ትችላለህና ። በመቀጠልም አደራ! ሰላትህን በሙሉ ልብ እና አላህን በውስጥ በመፍራት (በኹሹዕ) መስገድ አለብህ ። ይህም ባሪያው አላህ ፊት የሚቆምበት ዋነኛው አላማ ነውና ። የነቢዩን ﷺ የሶላት አሰጋገድ በገለፅኩልህ አኳኋን አላህን በመፍራት ከሳቸው የሶላት አሰጋገድ ጋር ባቀራረብክ ልክ አላህ በቁርዓኑ ያመላከተውን «ሶላት ከአፀያፊና ከመጥፎ ነገሮች ትጠብቃለች ።» የሚለውን ተከጃይ የሆነውን የሶላትን ፍሬ ያስገኝልሃል።

በመጨረሻም አላህ ሶላታችንና ሌሎች ስራዎቻችንን እንዲቀበለን እና ምንዳውንም እስከ ትንሳዔ ቀን («አላህን ሰላም በሆነ ልቡ የተገናኘ ሰው ሲቀር፤ ገንዘብና ልጅ የማይጠቅምበት ቀን ።») ድረስ እንዲሰበስብልን እለምነዋለሁ።

«ምስጋና ለአላህ ተገባው።»

# በሶላት ዙሪያ የሚያውጠነጥኑ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው[44]

**ጥያቄ፦** ሰውየው ከቂብላ ትንሽ ዘንበል ብሎ መስገዱን ከተገነዘበ ሰላቱን መድገም አለበትን?

**መልስ፦** ትንሽ ማዘንበል ጉዳት የለውም። ይህ የሚሆነው ከመስጂደል ሐራም ውጭ ለሚሰግድ ሰው ነው። በመስጂደል ሐራም ውስጥ ለሚሰግድ ሰው ቂብላው ከዕባ ራሱ ነው። ስለዚህ ዑለሞች "ካዕባን ማየት የሚመቸው ሰው ወደ ከዕባ ዞሮ መስገድ ግዴታ ይሆንበታል። ሰውየው በመስጂደል ሐራም ውስጥ እየሰገደ ወደ ከዕባ ሳይሆን ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞሮ ከሰገደ ሰላቱ ትክክል አይደለምና መድገም አለበት" ብለዋል። አላህ እንዲህ ይላል፦ "… ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ከዕባ) አቅጣጫ አዙር፣ የትም ስፍራ ብትሆኑም ስትሰግዱ ፊቶቻችሁን ወደርሱ አቅጣጫ አዙሩ።" [45]

ሰውየው ከካዕባ ርቆ ያለ ከሆነና ሊያየው ካልቻለ። መካ ውስጥ ቢሆንም እንኳ ወደ ካዕባ አቅጣጫ ዞሮ መስገድ አለበት። ትንሽ ማዘንበል ጉዳት የለውም። ለዚህም ነው ነብዩ ﷺ ለመዲና ሰዎች "በምስራቅና በምዕራብ መካከል ያለው (አቅጣጫ) ሁሉ ቂብላ ነው።" ያሉት[46]። የመዲና ሰዎች ወደ ደቡብ ዞረው ስለሆነ የሚሰግዱት በምስራቅና በምዕራብ መካከል ያለው አቅጣጫ ሁሉ ቂብላቸው ነው። እንደዚሁ ለምሳሌ ወደ ምዕራብ ዞረው ለሚሰግዱም በደቡብና በሰሜን መካከል ያለው አቅጣጫ ሁሉ ለነሱ ቂብላ ነው እንላለን።

**ጥያቄ፦** ሰፍን በማስተካከል ላይ የምንመረኮዝበት መሰረታዊ ነገር ምንድነው? ሰጋጁ ቁርጭምጭሚቱን አጠገቡ ካለው ሰው ቁርጭምጭሚት ጋር ማጋጠም ይችላልን?

**መልስ፦** ሰፍን ለማስተካከል የምንመረኮዝበት ቁርጭምጭሚት ነው እንጂ የእግር ጣትን አይደለም። ቁርጭምጭሚቶች መስመራቸውን እንዲጠብቁ አድርጎ መቆም ነው። ረጅም እና አጭር እግር እንዳለ ሁሉ ጣቶችም እንደ የሰው እግር ይበላለጣሉ። ስለዚህ የሰፍን ቀጥተኛነትና መስተካከል ያለ ቁርጭምጭሚት ማረጋገጥ ያስቸግራል። ቁርጭምጭሚትን አጠገብ ካለው ሰው ቁርጭምጭሚት ጋር ማጋጠምን በተመለከተ ሰሃቦች ያደርጉት እንደ ነበር ጥርጥር የለውም። ሰፋቸውን ያስተካክሉ የነበሩት ቁርጭምጭሚቶቻቸውን በማገጣጠም ነው። ሰፉ ቀጥ ብሎ እንዲስተካከል እያንዳንዱ ሰው ቁርጭምጭሚቱን አጠገቡ ካለው ሰው ቁርጭምጭሚት ጋር

---

[44] ይህ ክፍል የመጽሀፉ አካል አይደለም። ከተለያዩ የፈትዋ መፅሐፎች የተወሰደ የተረጓሚው ጭማሪ ነው።

[45] ከህይወት ፈተና፦የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፦ የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፦ ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[46] ከህይወት ፈተና፦የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፦ የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፦ ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

ያጋጥም ነበር። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ይህንን ማድረግ አለበት፡ ነገር ግን ይህ ማለት ቁርጭምጭሚቶች እስከመጨረሻው ተገጣጥመው ይቆዩ ማለት አይደለም። ዑለማዎች እንዳወሱት ቁርጭምጭሚትን ማገጣጠም በራሱ ተፈልጎ ሳይሆን ሰፍን ለማስተካከል ነውና።አንዳንድ ሰው ከልክ ያልፋል። ይኸውም እግሩን በሰፊው ከፍቶ ቁርጭምጭሚቱን አጠገቡ ካለው ሰው ቁርጭምጭሚት ጋር ያገጣጥምና በትከሻዎቻቸው መካከል ግን ሰፋ ያለ ክፍተት ይቀራል። ይህ የሱና ተቃራኒ ነው። የሚፈለገው ትከሻዎችና ቁርጭምጭሚቶች በትክክል ትይዩ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

**ጥያቄ፡-** በምሶሶዎች መካካል ቆሞ መስገድ እንዴት ይታያል?

**መልስ፡-** የቦታ ጥበት ባለ ጊዜ በምሶሶዎች መካከል ቆሞ መስገድ ይቻላል። የቦታ ጥበት ከሌለ ግን አይቻልም። ሶፍ ይቆራረጣልና።

ጥያቄ፡- ኒያን[47] በቃል መናገር እንዴት ይታያል?

**መልስ፡-** ነብዩ ﷺ «ሁሉም ስራዎች (የሚለኩት) በኒያ ነው። ሁሉም ሰው የነየተውን (ያሰበውን) ያህል ያገኛል።» ብለዋል[48]። የኒያ ስፍራ ልብ ነው። በቃል መናገር አያስፈልግም። ውዱዕ ለማድረግ ስትነሳ፤ ውዱዕ እንደምታደርግ አስበህ ነው። ይህ በራሱ ኒያ ነው። ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው እስካልተገደደ ድረስ ያለ ኒያ ስራ አይሰራም። ለዚህም አንዳንድ ኡለሞች «አላህ ያለ ኒያ ስራን እንድንሰራ ቢያስገድደን ኖሮ፤ መስራቱ የማይቻልን ነገር እንደ አስገደደን ይቆጠር ነበር።» ያሉት።

ነብዩም ﷺ ሆኑ ሶሀቦቻቸው ኒያን በቃላቸው ይናገሩ እንደነበረ አልተዘገበም። ኒያን ድምጻቸውን አሰምተው በቃላቸው የሚናገሩ ሰዎች፡- አንድም ባለማወቃቸው፤ ወይም ይህንን ይቻላል የሚሉትን ኡለሞች በመከተል ነው። እነዚህ ኡለሞች ልብና ምላስ እንዲስማሙ ለማድረግ ኒያን በቃል መናገር ተገቢ ነው ይላሉ። እኛ ግን ይህ አባባላቸው ትክክል አይደለም እንላለን። ይህ በሸሪዓ የተደነገገ ቢሆን ኖሮ ነብዩ ﷺ አንድም በድርጊታቸው ወይም በቃላቸው ለኡመታቸው ባብራሩ ነበርና።

ጥያቄ፡- ዱዓኡል ኢስቲፍታህ ሑክሙ ምንድ ነው?

---

[47] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[48] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

**መልስ፡-** ዱዓኡል ኢስቲፍታህ (የመክፈቻ ዱዓ) በፈርድም ሆነ በሱና ሶላት ውስጥ ሱና እንጂ ግዴታ አይደለም። ነብዩ ﷺ ሲጠቀሙበት ከነበሩት ዱዓዎች -አንድ ጊዜ አንዱን በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላኛውን- እያፈራረቁ መጠቀም የተወደደ ነው። የነቢዩን ﷺ ሱና በሁሉም መልኩ መተግበር አስፈላጊ ነውና። አንዱን ብቻ እንጂ ሌላውን የማያውቅ ከሆነና ሁሌም እሱኑ ብቻ የሚቀራ ከሆነም ችግር የለውም። ነቢዩ ﷺ ሶላት መክፈቻና በተሸሁድ ላይ የተለያዩ ዱዓዎችን ይጠቀሙ የነበሩት ለተከታዮቻቸው (ኡመታቸው) ለማግራት ነው። እንደዚሁም ከሶላት በኋላ ነብዩ ﷺ የተለያዩ ዚክሮችን (ውዳሴዎችን) ያደርጉ ነበር። ይህም ለሁለት ጥቅም ነው።

አንደኛው፡- ሰው በአንድ አይነት ዱዓ ወይም ዚክር ላይ እንዳይዘወትር ነው። ሰው በአንድ ዓይነት ዚክር ላይ ከዘወተረ ነገሩ የተለመደ ይሆናል። ከተለመደ ደግሞ ዚክሩን ለማለት ሳይፈልገውም ይለዋል። የተለመደ ስለሆነ ሳያስበው በምላሱ ሊዘክር ይችላልና። ዚክሮቹ የተለያዩ ከሆኑና ሰውየው አንድ ጊዜ አንዱን በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላውን ከዘከረ ግን ልቡም ነቃ ብሎና ትርጉሙንም እያስተነተነ ይዘክራል።

ሁለተኛውን፡- ለኡመቱ ለማግራት ነው። ሰው እንዳስፈላጊነቱ እየለዋወጠ ዚክር ማድረግ እንዲችል ነው። ለነዚህ ሁለት ጥቅሞች ሲባል አንዳንድ ዒባዳዎች ለምሳሌ፡- የመክፈቻ ዱዓ፣ በተሸሁድ ላይ የሚደረግ ዱዓ እና ከሶላት በኋላ የሚደረጉ ዚክሮች በተለያየ መልኩ ነብዩ ﷺ ያደርጉ ነበር።

**ጥያቄ፡-** ቀኝ እጅን በግራ እጅ ላይ አድርጎ ደረት ላይ ወይም ልብ ላይ ማድረግ ሑክሙ ምንድነው? ከእምብርት በታች ማድረግስ ሑክሙ ምንድነው? በዚህ ላይ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት አለ?

**መልስ፡-** በሶላት ውስጥ ቀኝ እጅን በግራ እጅ ላይ ማድረግ ሱና ነው። ይህን በተመለከተ ሰህል ቢን ሰዕድ እንዲህ ይላል፡- "ሰዎች ሶላት ውስጥ ቀኝ እጃቸውን በግራ ክንዳቸው ላይ እንዲያደርጉ ይታዘዙ ነበር።"[49] ነገር ግን የት ነው የሚደረገው? ለሚለው፡- ወደ ሰሂህነት (ትክክለኛነት) ይበልጥ የሚቀርበው አስተያየት ደረት ላይ ማድረጉ ነው። ዋኢል ቢን ሐጀር "ነቢዩ ﷺ ቀኝ እጃቸውን በግራ እጃቸው ላይ ያደርጉና በደረታቸው ላይ ያኖሩ ነበር" ብሏልና።[50] ሐዲሱ ሰነዱ ላይ ደዒፍነት (ድክመት) ያለበት ቢሆንም ከርሱ ሌላ ያለው ቢድዓ ነው፤ መሰረት የለውም። ከእምብርት በታች ማድረግን በተመለከተ ዐሊይ ያደርጉ እንደነበረ ተዘግቧል። ነገር ግን ዘገባው ደዒፍ ነው። የዋኢል

---

[49] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[50] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

ቢን ሀጀር ሐዲስ ከሱ ይጠነክራል። በዚህ ሑክም ላይ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት የለም። የሚለያቸው ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ሴቶችና ወንዶች በአህካም ላይ እኩል ናቸው። በዚህ ሱና ላይ ወንድና ሴትን የሚለይ ትክክለኛ ማስረጃ አላውቅም።

**ጥያቄ፡-** በሶላት ውስጥ ቁርዓን ሲቀራ፡- ድምጽን አሰምቶ «ቢስሚላህን» መቅራት ሁክሙ ምንድን ነው?

**መልስ፡-** ሚዛን የሚደፋው (ራጂህ)አስተያየት «ቢስሚላህን» ድምጽን ከፍ አድርጎ መቅራት ተገቢ አለመሆኑ ነው። ሱናው ድምፅን ሳያሰሙ መቅራት ነው። የፋቲሃ አካል አይደለምና። ነገርግን አንዳንድ ጊዜ ድምጽ አውጥቶ ቢቀራ ችግር የለውም። እንደውም አንዳንድ ኡለሞች አልፎ አልፎ ደምጽን በማሰማት መቅራት ይገባል። ነብዩ ﷺ ድምጽ አውጥተው ይቀሩ እንደነበረ ተዘግቧልና ይላሉ።[51] ነገር ግን ከነብዩ ﷺ በርግጠኝነት የተዘገበው ድምጽ አውጥተው እንደማይቀሩ ስለሆነ ድምጽ አውጥቶ አለመቅራቱ ይመረጣል።

**ጥያቄ፡-** ሶላት ውስጥ ማእሙሙ ፋቲሃን የሚቀራው ኢማሙ ፋቲሃ ሲቀራ ነው ወይስ ኢማሙ ሌላውን ሱራ ሲቀራ ነው?

**መልስ፡-** ግዴታ እና ማእዘን የሆነው ፋቲሃ ሲቀራ ማዳመጥ ስለሚያስፈልግ ፋቲሃን መቅራት ኢማሙ ከቀራ በኋላ ቢሆን ይመረጣል። ኢማሙ እየቀራ አብሮት ቢቀራ ሩክን የሆነውን ፋቲሃ አላዳመጠም፤ ያዳመጠው ሱና የሆነውን ከፋቲሃ በኋላ ኢማሙ የቀራውን ምእራፍ ነው ማለት ነው። በላጩ ፋቲሃን ማዳመጥ ነው። ሩክን የሆነውን ማዳመጥ ሱና የሆነውን ከማዳመጥ ይበልጣልና። ይህ በአንድ ወገን ሲሆን በሌላ ወገን ስናይ ደግሞ ኢማሙ “ወለድዳሊን” ሲል አንተ ተከታትለህው “አሚን” ማለት አትችልም። ይህ ከሆነ ደግሞ ከጀማዓ ትወጣለህ። ስለዚህ በላጩ ኢማሙ ከቀራ በኋላ መቅራቱ ነው።

**ጥያቄ፡-** ሰውየው ኢማሙ ፋቲሃን ከጨረሰ በኋላ ቢደርስ እና ኢህራም አድርጎ ፋቲሃን መቅራት እንደ ጀመረ እሱ ፋቲሃንውን ሳይጨርስ ኢማሙ ሩኩዕ ቢወርድ፤ ይህ ሰው ኢማሙን ተከትሎ ሩኩዕ መውረድ አለበት ወይስ ፋቲሃን መጨረስ አለበት?

**መልስ፡-** ኢማሙ ሩኩዕ ለመውረድ ሲል ማዕሙሙ ከደረሰና ሙሉ ፋቲሃን መቅራት ካልተመቸው ከሁለት ሁኔታዎች ውጭ ሊሆን አይችልም። አንደኛው ከፋቲሃ የቀረው አንድ ወይም ሁለት አንቀጽ ከሆነ እና ፋቲሃውን ጨርሶ ኢማሙን በሩኩዕ ላይ ሊደርስበት የሚችል ከሆነ ፋቲሃውን ቢጨርስ ይመረጣል። የቀረው ብዙ ከሆነ እና ኢማሙን በሩኩዕ ላይ የማይደርስበት ከሆነ ፋቲሃውን ባይጨርሰውም ሩኩዕ መውረድ አለበት።

**ጥያቄ፡-** “ኣሚን” ማለት (ተእሚን) ሱና ነውን?

---

[51] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

*መልስ፡- አዎን "ኣሚን" ማለት የጠበቀ ሱና ነው። በተለይም ኢማሙ ኣሚን ካለ። ከአቡሁረይራ በተላለፈው ሐዲስ ነብዩ ﷺ "ኢማሙ ኣሚን ካለ ኣሚን በሉ። የርሱ ተእሚን (ኣሚን ማለት) ከመላኢካ ተእሚን ጋር የተገጣጠመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል።" ብለዋል።[52] የኢማሙና የማእሙሙ ተእሚን በአንድ ጊዜ መሆን አለበት። ነብዩ ﷺ "ኢማሙ "ወለድዳሊን ሲል "ኣሚን" በሉ ብለዋልና።[53]*

**ጥያቄ፡-** *እናቴ ሶላትን ትሰግዳለች ነገር ግን በተሟላ መልኩ አትሰግድም። ምክንያቱም እሷ የምታውቀው ፋቲሃን ብቻ ነው። ሳስተምራት ቶሎ ትረሳለች። ሶላቷ ተቀባይነት አለው?*

**መልስ፡-** ሶላቷ ተቀባይነት አለው። በአንቺና በወንድሞችሽ ላይ እናታችሁ ተገቢውን እወቀት እስክታገኝ ድረስ በአቅማችሁ ያህል የማስተማር ግዴታ አለባችሁ። ፋቲሃ በቂ ቢሆንም እናታችሁን አጫጭር ሱራዎችን እንደ ‹‹ቁልሁወላሁ አሀድ››፤ ‹‹ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ›› እና ‹‹ቁል አዑዙ ቢረቢናስ›› ብታስተምሯትና መሀፈዝ (መሸምደድ) ብትችል በጣም የተሻለ ነው። በአላህ ፍቃድ በተደጋጋሚ ካስተማራችኋት ትይዛለች። ፋቲሃንም እንኳ የማያውቅ ሰው ሶላቱ ተቀባይነት አለው። እንዲህ አይነት ሰው የሚችለውን የቁርዓን አንቀጽ ይቀራል። ምንም የማይችል ከሆነ ቁርዓን በሚቀራበት ቦታ ሁሉ ‹‹ሱብሃነላህ››፣ ‹‹ወለወሀምዱ ሊላህ››፣ ‹‹ወላኢላሀ ኢለሏህ››፣ ‹‹ወላሁ አክበር›› በማለት ሩኩዑን ያደርጋል። አላህ ብሏልና «የምትችሉትን የቁርዓን አንቀጽ ቅሩ።»፤ «ያአቅማችሁን ያህል አላህን ፍሩት።» መልዕክተኛውም< ሶላቱን ያበላሸው ሰውዬ አስተምሩኝ ሲላቸው «... ከዚያም የምትችለውን የቁርዓን አንቀጽ ቅራ።» እንዲሁም ለዚያ ቁርዓንን መቅራት ለማይችለው ሰውዬ ደግሞ «ሱብሃነላህ፣ ወልወሀምዱ ሊላህ፣ ወላኢላሀ ኢለሏህ፣ ወላሁ አክበር፤ ወላሀውለ ወላቁወተ ኢላቢላሂል አሊዩል አዚም።» በል ብለዋልና። ሶላትን ሙሉ በሙሉ መተው በፊጹም አይቻልም። ስለዚህ ሁሉም አላህን ፈርቶ በአቅሙ ያህል ለመማር እየጣረ መስገድ አለበት። የሚያውቁ ሰዎች ልጅ፣ ዘመድም ሆነ ባዕድ የሚያውቁትን የማስተማር ግዴታ አለባቸው። አላህ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ብሏልና፡- «በጥሩ ስራ እና በአላህ ፍራቻ ላይ ተጋገዙ።»54 እንዲሁም «በጊዜያት

---

[52] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[53] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[54] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

እምላለሁ የሰው ልጅ በክስረት ላይ ነው ያለው። አነዚያ ያመኑ፣ ደግን ስራ የሰሩ፣ በእውነት እና በትዕግስት ላይ አደራ የተባባሉ ሲቀሩ።» 55

ጠያቂ እህት ሆይ አንቺና ወንድሞችሽ እንዲሁም ሌሎች ዘመዶቻችሁ ተባብራችሁ እናታችሁን በትዕግስት፣ በጥሩ ንግግር፣ ተስማሚ ጊዜና አካሄድ በመጠቀም በተደጋጋሚ ሳትሰለቹ አስተምሯት ። ይህች የቅርቢቱ አለም የስራ፣ የመጠቃቀሚያ እና የመደጋገፊያ ሀገር ናት ። አላህ ሁሉንም ቅኑን መንገድ እንዲመራ ጸሎታችን ነው።

ጥያቄ፡- በሶላት ውስጥ አይንን መጨፈን እንዴት ይታያል?

መልስ፡- በሶላት ውስጥ አይንን መጨፈን የተጠላ (መክሩህ) ነው። ነቢዩ< ሲሰግዱ ከነበረበት ስርዓት የተለየ ሁኔታ ነውና። ለበቂ ምክንያት ለምሳሌ፡- ግድግዳ ወይም ምንጣፍ ላይ ጌጣጌጥ ወይም ለአይን የሚከብድ ሀይለኛ የመብራት ጨረር ካለ ወይም ለሌላ አሳማኝ ምክንያት ከሆነ አይንን መጨፈን ችግር የለውም ። ያለ ምክንያት ግን የተጠላ ነው።

**ጥያቄ፡-** ሰላትን በ«ኹሹዕ»56 እንዴት መስገድ እንችላለን? በሰላት ውስጥ ቁርአን ስንቀራም ሆነ ከቁርአን ውጭ "ኹሹዕ" ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው?

**መልስ፡-** "ኹሽዕ" የሰላት ልብና አስኳሉ ነው። "ኹሽዕ" ማለት ልብን ሰብሰብ አድርጎ መስገድ ማለት ነው ። ሰውየው "ኹሽዕ"ን የሚያፋልስበት ነገር ልቡ ላይ ከመጣበት ከተረገመው ሰይጣን "አዑዙቢላህ ሚነሽይጣንርረጂም" በማት በአላህ ይጠበቅ። ነቢዩﷺ ይህን አዘዋልና[57]። ሰይጣን ሁሉንም የሰው ኢባዳዎች በተለይም ከ‹ሸሃደተይን› ቀጥላ ከሁሉም ዒባዳዎች በላጭ የሆነችውን ሶላት ዋጋ ለማሳጣትና ውድቅ ለማድረግ

---

[55] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[56] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

[57] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

በጣም እንደሚጎዳ ጥርጥር የለውም። ወደ ሰጋጁ ይመጣና ይህን አስታውስ ያን አስታውስ ይለዋል[58]። ሰውየው ልቡን ወደ አላህ ለማዞር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል። በሶላቶቹ ውስጥ እነዚህ ወስዋሶች ከተከሰቱበት ሩኩዕ ላይም ይሁን ሱጁድ ተቀምጦ ወይን ቆሞ “አዑዙቢልላህ ሚነሸሸይጣኒርረጂም” ይበልና ከሰይጣን በአላህ ይጠበቅ። በሰላቱ ውስጥ “ኹሹዕ” እንዲኖረው ከሚረዱት ነገሮች በላጩ አላህ ፊት በመቆም ላይ መሆኑንና አላህን ለብቻው ሆኖ እያነጋገረው መሆኑን ልቡ እንዲያውቅ ማድረግ ነው።

**ጥያቄ፦** ነቢዩ ﷺ በፋቲሃና በሌላ ሱራ መካከል ዝም ይሉ እንደነበረ ተዘግቧልን?

**መልስ፦** በፋቲሃና በሌላ ሱራ መካከል የሚደረገው ዝምታ ከነቢዩ< አልተገኘ። ሆኖም አንዳንድ ፉቀሃኦች59 ማእሙም ፋቲሃን ለመቅራ እንዲያመቸው ኢማሙ ትንሽ ዝም ይበል ይላሉ ። ይህም ለኢማሙም ትንፋሹን ለማረጋጋና ለማእሙም ፋቲሃ እንዲቀራ በር ለመክፈት ነው ። መቅራቱን ጀምሮ ኢማሙ ሌላ ሱራ መቅራት ከጀመረ በኋላም ቢሆን ሊጨርሰው ይችል ዘንድ ረዥም ሳይሆን ትንሽ ዝምታ ያስፈልጋል ይላሉ ።

**ጥያቄ፦** አንድ ሰው ጀምዓ ሶላት ሊሰግድ ሲመጣ ኢማሙ ሩኩዕ ላይ እያለ ቢደርስበት ሁለቴ ተክቢራ ማድረግ አለበትን?

**መልስ፦** ሰውየው ኢማሙ ሩኩዕ ላይ እያለ ከገባና ለኢህራም ተክቢራ ካደረገ በኋላ ለሩኩዕ ተክቢራ ቢያደርግ ጥሩ ነው። ነገርግን የሩኩዕ ተክቢራ ሱና ስለሆነ በእንደዚህ ያለ ግዜ ቢተውም ችግር የለውም ።

**ጥያቄ፦** በሶላት ውስጥ የተወሩክ ሑክም ምንድነው? ለወንድና ለሴት እኩል ነውን?

**መልስ፦** ሁለት ተሸሁድ ባላቸው እንደ መግሪብ ፣ዒሻእ ፣ ዙህርና ዐስር ሰላቶች በመጨረሻቸው ተሸሁድ ላይ የተወሩክ አቀማመጥ ሱና ነው። አንድ ተሸሁድ ብቻ ያለው ሶላት ግን ኢፍትራሽ እንጂ ተወሩክ የለውም። ለወንድና ለሴት እኩል ነው ወይ ለተባለው ደግሞ “አዎን” ነው ። ለወንድም ሆነ ለሴት እኩል ነው። በመሰረቱ በሸሪዓዊ አህካሞች እኩል አለመሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ወንድና ሴት እኩል ናቸው። በአሰጋገድ ሁኔታዎች ላይ ወንድና ሴት እንደሚለያዩ የሚያመለክት ትክክለኛ የሆነ ሸሪዓዊ ማስረጃ ደግሞ የለም። ስለዚህ ለሁለቱም እኩል ነው።

**ጥያቄ፦** ለዚክር “ሚስበሃ” (የዚክር መቁጠሪያ)ን መጠቀም እንዴት ያዩታል?

---

58 ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

59 ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

**መልስ፡-** ሚስበሃን መጠቀም ይቻላል። ነገር ግን በላጩ በጣቶች ዚክር ማድረግ ነው። ነቢዩﷺ "በጣቶቻችሁ እየቆጠራችሁ ዚክር አድረጉ (የውመልቂያማ) ተጠይቀው ይናገራሉና" ብለዋልና።[60] ሚስበሃን መሸከም ሪያእ (ይዩልኝ ባይነት) ሊኖርበትም ይችላል። በሚስበሃ ተስቢህ ወይም ዚክር የሚያደረግ ሰው ብዙውን ጊዜ በልቡ ሳያስብ (ኒያ ሳይኖረው) ግራና ቀኝ እየተመለከተ ዚክር ያደርጋል። ጣትን መጠቀም ነው በላጩና የሚሻለው።

ጥያቄ፡- ከሰላምታ በኋላ የሚደረጉ አዝካሮች ምን ምን ናቸው?

**መልስ፡-** ከሶላት በኋላ ያለውን ዚክር አላህ በቁርዓኑ አዟል።

(فَإِذَا قَضَيْتُمُ الصَّلَاةَ فَاذْكُرُوا اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَى جُنُوبِكُمْ) النساء ١٠٣

«ሶላትን በጨረሳችሁ ጊዜ ቆማችሁም፣ ተቀምጣችሁም፣ በጎናችሁ ተጋድማችሁም አላህን አውሱት።» (አል-ኒሳዕ፡ - 103)

አላህ በጥቅሉ ያዘዘበትን ይህን ዚክር ነብዩ ﷺ በግልጽ አብራርተውታል። እናም ከሰላምታ በኋላ የሚከተሉት ዚክሮች ይባላሉ።

ሶስት ጊዜ፡ أستغفر الله -አስተግፊሩላህ።

«አላህ ምህረት እንዲያደርግልኝ እለምናለሁ፡»

ከዚያም፡-

اللهم أنت السلام ، ومنك السلام ، تباركت يا ذا الجلال والإكرام

‹‹አላሁመ አንተ ሰላም ወሚንከ ሰላም ተባረክተ ያ ዘልጀላሊ ወል- ኢክራም»

«አላህ ሆይ! ሰላም አንተ ነህ፤ ሰላም ከአንተ ነው፤ የግርማዊነትና የክብር«‹ ባለቤት የሆንክ ሆይ! ልቅና ተገባህ።»

لا إله إلا الله وحده لا شريك له ، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير

«ላ-ኢላሀ ኢለ-ሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሽይኢን ቀዲር»

«ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ብቸኛ ነው፤ አጋርም የለውም፤ ንግስና የሱ ነው፤ ምስጋና ይገባው፤ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው።»

اللهم لا مانع لما أعطيت، ولا معطي لما منعت، ولا ينفع ذا الجد منك الجد

***(አላሁመ ላ ማኒአ ሊማ አዕጠይት ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕት ወላ የንፈኡ ዘልጀዲ ሚንከል ጀድ)***

---

[60] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

«አላህ ሆይ! አንተ ለሰጠኸው ነገር ከልካይ የለም፤ ለከለከልከውም ነገር ሰጪ የለም፤ የሀብት ባለቤትም አይጠቅምም ሀብት ከአንተ ነውና፡፡»

لا إله إلا الله، ولا نعبد إلا إياه ، له النعمة وله الفضل وله الثناء الحسن ، لاحول ولا قوة إلا بالله ،لا إله إلا الله، ولا نعبد إلا إياه ،مخلصين له الدين ولو كره الكافرون

«ላኢላ*ሀ* ኢለ-ሏል፣ ወላ ነዕቡዱ ኢላ ኢያሁ ፤ለሁ ኒዕመቱ ወለሁል ፈድሉ፤ ወለሁል ሰናኡል-ሀሰን፣ ላ ሀውለ፣ ወላ ቁወተ ኢላ ቢል-ላህ፡፡ ላ ኢሏ*ሀ* ኢለ-ሏህ፣ ወላ ነዕቡዱ ኢላ ኢያሁ፣ ሙክሊሲነ ለሁዲነ ወለው ከሪሀል ካፊሩን፡፡»
«ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ከርሱ በስተቀር ሌላን አንገዛም፡፡ ጸጋ የሱ ነው፤ ችሮታም የሱ ነው፤ ጥሩ ውዳሴ የሱ ነው፡፡ በአላህ ካልሆነ መላም ሀይልም የለም፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ካህዲያን ቢጠሉትም ሀይማኖትን ለሱ አጥርተን እርሱን በስተቀር ሌላን አንገዛም፡፡»
ከዚያም ሰላሳ ሶስት ጊዜ፡ -

سبحان الله ، والحمد لله، والله أكبر

«ሱባሃነላህ፣ ወል ሀምዱ ሊላህ፣ ወላሁ አክበር›› ማለት፡፡
«ጥራት ለአላህ ይገባው፡፡››፤ ‹‹ምስጋና ለአላህ ነው፡፡››፤ ‹‹አላህ ታላቅ ነው፡፡»
ከዚያም መቶኛ፡-

لا إله إلا الله وحده لا شريك له ، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير

«ላኢላሀ ኢለሏህ፣ ወህደሁ፣ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ፣ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ አላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፡፡»
«ሱባሃነላህ፣ ወልሀምዱ ሊላህ፣ ወላሁ አክበር›› የሚለውን አንድ ላይ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ብትልም ወይም ለየብቻው ‹‹ሱባሃነላህ›› ሰላሳ ሶስት ጊዜ ፤ ‹‹ወልሀምዱ ሊላህ›› ሰላሳ ሶስት ጊዜ፤ ‹‹አላሁ አክበር›› ሰላሳ ሶስት ጊዜ ማለትም ትችላለህ፡፡ ሰላሳ ሶስት፣ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ማለቱን ትተህ አስር አስር ጊዜም ማድረግ ትችላለህ፡፡
ወይም ደግሞ በዚህ ምትክ የሚከተሉትን አራት ዚክሮች ሀያ አምስት ጊዜ ማለት ትችላለህ፡፡ በአንድ ላይ መቶ ይሆናል ማለት ነው፡፡

سبحان الله، والحمد لله، و لا إله إلا الله، والله أكبر

«ሱባሃነላህ፣ ወልሀምዱሊላህ፣ ወላኢላሀ ኢለ-ሏህ፣ ወላሁ አክበር»
ከነዚህ ከተጠቀሱት ዚክሮች የፈለከውን መጠቀም ትችላለህ፡፡ ምክንያቱም በሸሪዓዊ መርህ በተለያየ መልኩ የተላለፉ ኢባዳዎችን ሁሉንም እየለዋወጡ በተለያየ ጊዜ መጠቀም ሱና ነውና፡፡ ሱናን በሁሉም መልኩ መፈጸም አስፈላጊ ነውና፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ዚክሮች በሁሉም ሶላቶች የሚደረጉ አጠቃላይ ዚክሮች ናቸው፡፡ በመግሪብና በሱብሂ ሶላት ላይ፡-

لا إله إلا الله وحده لا شريك له، له الملك وله الحمد، يحي ويميت وهو على كل شيء قدير

«ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ዩህዩ ወዩሚቱ ወሁወ አላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር»

የሚለውና ‹‹ረቢ አጅርኒ ሚነ ናር›› ‹‹ጌታዬ ከዕሳት ጠብቀኝ›› የሚለውን አስር አስር ጊዜ ማለት ያስፈልጋል።
**ጥያቄ፡-** በአንዳንድ አገሮች ከፈርድ ሰላቶች በኋላ በህብረት (በጀማዓ) ፋቲሃና ‹ኣየተል ኩርሲይ›ን ይቀራሉ፣ ሌላም ዚክር ያደርጋሉ። ሑክሙ ምንድነው?
**መልስ፡-** ከሰላት በኋላ በጀማዓ (በአንድነት) ድምፅ ከፍ አድርጎ ፋቲሃንና ‹ኣየተል ኩርሲ›ን መቅራትና ዚክር ማድረግ ቢድዓ ነው። ነቢዩ ﷺ እና ሰሃቦቻቸው ከሶላት በኋላ ከፍ ባለ ድምፅ ዚክር ያደርጉ ነበር። ነገር ግን በጋራ ሳይሆን ሁሉም ለየብቻቸው ነበር የሚያደርጉት። ከፈርድ ሰላት በኋላ ድምፅን ከፍ አድርጎ ዚክር ማድረግ ሱና ነው። ኢብኑ ዐባስ "በነቢዩ ﷺ ዘመን ፈርድ ሶላት ተሰግዶ ሲያበቃ ድምፅ ከፍ ተደርጎ ዚክር ይደረግ ነበር "ብሏል።[61]
ከሶላት በኋላ ፋቲሃን መቅራት በተመለከተ ግን ያለድምፅም ሆነ ድምፅን ከፍ አድረጎ እንደሚቀራ የሚያመለክት ከነቢዩ ﷺ የተላለፈ ሐዲስ መኖሩን አላውቅም። ከነቢዩ ﷺ የተላለፈው ከሶላት በኋላ ‹ኣየተል-ኩርሲን›፣ ‹ቁልሁወላሁ አሀድን›፣ ‹ቁል-አኡዙ ቢረቢል ፈለቅ›ን እና ‹ቁል-አኡዙ ቢረቢ ናሲን› መቅራት እንደሚቻል የሚያመለክት ብቻ ነው።
**ጥያቄ፡-** ሶላት ሲጠናቀቅ በመጨባበጥ «አላህ ይቀበለን» መባባል እርሶ እንዴት ያዩታል?
**መልስ፡-** ከሶላት በኋላ መጨባበጥ እና «አላህ ይቀበለን» መባባል ምንም መሰረት የለውም። ከነብዩ ﷺ ሆነ ከሶሃቦች ይህንን ስለማድረጋቸው አልተዘገበም።
**ጥያቄ፡-** ሱጁዱ ሰህው- የሚያስወርዱ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
**መልስ፡-** ለሱጁዱ ሰህው ሶስት ምክንያቶች አሉት። እነሱም መጨመር፣ መቀነስ እና ጥርጣሬ ናቸው ።
**መጨመር፡-** የዚህ ምሳሌው አንድ ሰው በሶላቱ ውስጥ ሩኩዕን ሲጨምር (ማለትም በአንድ ረከዓ ላይ ሁለቴ ሩኩዕ ሲያደርግ) ወይም ሱጁድን ሲጨምር (በአንድ ረከዓ ሶስቴ ሱጁድ ሲያደርግ) ወይም ሌላ የሶላት ማዕዘን ወይም ዋጂብ ሲጨምር ነው። በእንደዚህ አይነት ጊዜ ካሰላመተ በኋላ ሱጁዱ ሰህው ይወርዳል። ማለትም ተሸሁድ ይልና ያሰላምታል። ከዚያም ሁለት ሱጁድ አድርጎ እንደገና ያሰላምታል። መልዕክተኛው ﷺ አምስት ረከዓ ሰግደው ሰሃቦች ሲያስታውሷቸው ሁለት ሱጁድ ከሰላምታ በኋላ ሰግደዋል። በአንድ ወቅት ነብዩ ﷺ ከዙህር ወይም ከአስር ሶላቶች

61 ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

አንዱን እየሰገዱ ከሁለተኛው ረከዓ በኋላ አሰላመቱ። ከዚያም ሰሀቦች ሲያስታውሷቸው የቀሩትን ሁለቱን ረከዓ ሞሉና አሰላመቱ። ቀጥሎም ሁለት ስጁዶችን ሰግደው አሰላመቱ።[62]

**መቀነስ፡-** ከሶላት ግዴታዎች ወይም ማዕዘኖች ሲቀነስ ነው። የዚህ ሱጁድ ከሰላምታ በፊት ነው። ምሳሌ ተሸሁድን ረስቶ ቆመ፤ በሩኩዕ ላይ ሱብሃነ ረቢየል-አዕላ ማለትን ረሳ፤ በእንዲህ ጊዜ ሳያሰላምት ሱጁዱ ሰህው ይሰግዳል። ይህን ግዴታ በመተው ሶላቱ ተጓድሏልና ከመሰላመቱ በፊት ሁለት ሱጁድ መስገዱ ሶላቱ ከመጠናቀቁ በፊት ይህን ጉድለት ለመጠገን ነው። የአብደላ ብን ሁየይና ያስተላለፈው ሀዲስ ለዚህ መረጃ ነው። «ነብዩ ﷺ ዙህርን ሲሰግዱ የመጀመሪያውን ተሸሁድ ሳይቀመጡ ተነሱ። ሶላትን ሲጨርሱ ሰዎች ሰላምታን ያደርጋሉ ብሎ ሲጠብቁ በተቀመጡበት አላሁ አክበር ብለው ሁለት ሱጁዶችን ሰገዱ ከዚያም አሰላመቱ።»

**ጥርጣሬ፡-** ጥርጣሬ ማለት ጉድለቱን ወይም ጭማሪ መሆኑን መጠራጠር ነው። ለምሳሌ ሶስት ረከዓ ሰገድኩ ወይስ አራት ብሎ መጠራጠር። እንዲህ አይነቱ በሁለት ይከፈላል።

አንደኛው፡- አንዱ ጥርጣሬ ማለትም መጉደሉ ወይም መጨመሩ አመዝኖ ሲገኝ። ይህ ከሆነ ጥርጣሬ ወዳመዘነው በማዘንበል የተቀረውን ሶላቱን ይሞላል። ከዚያም ካሰላመተ በኋላ ሱጁዱ ሰህው ያደርጋል። ለዚህ መረጃው ኢብን መስዑድ ባስተላለፉት ሀዲስ ነብዩﷺ አሉ፡- «አንዳችሁ በሶላት ውስጥ ከተጠራጠረ፤ ጥርጣሬው ወደ ሚያመዝንበት ተሞርክዞ ሶላቱን ይጨርስ። ከዚያም ይሰላመት። ከሰላምታ በኋላ ሁለት ሱጁድ ይስገድ።»

ሁለተኛው፡- ሁለቱም ጥርጣሬዎች እኩል ከሆኑ እርግጠኛ በሆነበት ማለትም በትንሹ ላይ ይወሰንና ሶላቱን ይሞላል። ከዚያም ከማሰላመቱ በፊት ሱጁዱ ሰህው ያደርጋል። የመልዕክተኛውﷺ ፈለግ የሚያመለክተው ይህንን ነው።

ስለዚህ፡-ሱጁዱ ሰህው ከሰላምታ በፊት የሚሆነው አንድን ዋጂብ ከተወ ወይም በረከዓ ብዛት ከተጠራጠረና ከጥርጣሬው አንዱ ካላመዘነ ነው። በሶላት ላይ ከጨመረ ወይም ጥርጣሬ ኖሮ አንዱ ጥርጣሬ ካመዘነ ግን ሱጁዱ ሰህው ከሰላምታ በኋላ ይሆናል።

**ጥያቄ፡-** አንድ ሰጋጅ ሶስት ወይም አራት ረከዓ መስገዱን ከተጠራጠረ ምን ማድረግ አለበት ?

**መልስ፡-** በጥርጣሬ ግዜ እርግጠኛ ከሆነበት ይነሳና የቀረውን ይሞላል ። ከላይ ለተገለጸው ጥያቄ ሶስት ወይም አራት ረከዓ መስገዱን ከተጠራጠረ ሶስት ረከዓ ለመስገዱ እርግጠኛ ነውና ሶስት እንደሰገደ አስቦ አራተኛውን መጨመር አለበት። ከዚያም ከማሰላመቱ በፊት ተጨማሪ ሁለት ስጁድ (ስጁዱ ሰህው) ይሰግዳል። ለዚህም መረጃችን፡- «አንዳችሁ በሶላት ውስጥ ሶስት ወይም አራት ረከዓ መስገዱን ከተጠራጠረ የሚያጠራጥረውን

---

[62] ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

ይተውና እርግጠኛ በሆነበት ላይ ይሙላ። ከዚያም ከማሰላመቱ በፊት ሁለት (ተጨማሪ) ሱጁዶችን ያድርግ። የሚለው ሙስሊም የዘገበው የመልዕክተኛው ﷺ ንግግር ነው።

ከሁለቱ ጥርጣሬዎች ወደ አንደኛው ካመዘነ ደግሞ በጣም በጠረጠረው ላይ ተሞርክዞ ይስገድና ከዚያም ከሰላምታ በኋላ ሁለት ስጁዶችን ያድርግ። መልዕክተኛው ﷺ ይህን በማስመልከት የሚከተለውን ብለዋልና።

«አንዳችሁ በሶላታችሁ ላይ ከተጠራጠራችሁ ይበልጥ በሚጠረጥረው ላይ ተሞርክዞ ይስገድ። ከዚያም ከተሰላመተ በኋላ ሁለት ስጁድ ይስገድ።»[63]

**ጥያቄ፡-** አንድ ሰው የመጀመሪያውን ‹ተሸሁድ› ቢረሳና (ጉድለቱን ለሟሟላት ሚሰገደውን) ሱጁዱ ሰህውንም ቢረሳ ምን ማድረግ አለበት?

**መልስ፡-** እንደ አሰላመተ ካስታወሰ ሱጁዱ ሰህውን ይስገድ። ነገርግን ብዙ ከቆየ በኋላ ካስታወሰ ምንም ማድረግ የለበትም። ሶላቱም ትክክል ነው። በትክክኛው የኡለሞች አስተያየት መሰረት።

**ጥያቄ፡-** ኢማሙ ረስቶ አንድ ረከኣ ከጨመረና እኔ ደግሞ ተቀድሜ ስለነበር በዚያ በተጨመረው ረከኣ ሶላቴን ብሞላ ሶላቴ ትክክል ይሆናልን? በሱ ብቻ ሳልወሰን አንድ ረከኣ ብጨምርስ?

**መልስ፡-** በትክክለኛው አስተያየት የአንተ ሶላት ትክክል ነው። የሰገድከው ሙሉ ነውና። የኢማሙ ጭማሪ ለራሱ ነው። እርሱ ረስቶ ስለሆነ አይጠየቅበትም። እርሱ ከጨረሰ በኋላ አንተ ተነስተህ ብትጨምር ደግሞ ያለ ምንም ምክንያት አንድ ረከዓ ስለጨመርክ ሶላትህ ይበላሻል።

**ጥያቄ፡-** ሰውየው በፈጅር ሶላት (ከጀማዓ) አንድ ረከዓ ቢያመልጠው ኢማሙ ካሰለመተ በኋላ ተነስቶ ሲሞላ ድምፁን አሰምቶ ነው ወይስ ሳያሰማ መቅራት ያለበት?

**መልስ፡-** ምርጫ አለው ። ነገር ግን በላጩ ድምፁን ሳያሰማ መቅራቱ ነው። ምክንያቱም ሌላም ሰው እንደሱ ሶላቱን የሚሞላ ስለሚኖር ሊረብሸው ይችላልና።

**ጥያቄ፡-** በሚሰግድ ሰው ፊት ማለፍ ሶላትን ይቆርጣልን? የሚያልፈው ሰው ወንድም ወይም ሴት፣ ዘመድ ወይም ባዕድ ቢሆን ልዩነት አለውን?

**መልስ፡-** ወንድ ማለፉ የሴትን ሶላት አያበላሽም። ነገርግን በሰጋጅ ፊት ወይም በሱና በከለላው (ሱትራው) መሀል ማለፍ ለማንም አይፈቀድም፤ ሰጋጁ ወንድም ሆነ ሴት። ሶላትን የሚቆርጡት ለአቅመ አዳም የደረሰች ሴት፣ አህያ፣ እና ጥቁር ውሻ ናቸው። በዚህ ላይ አቡ ሁረይራ፣ አቡ ዘርና ኢብን አባስ ያስተላለፉት ሶሂህ ሀዲስ አለ።

---

63 ከህይወት ፈተና፡-የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሚፈተንባቸው ገንዘብ እና መጥፎ ስሜትን መከተል የመሳሰሉት ። የመሞት ፈተና፡- የቀብር ፈተና እና የመላዕክቶች ጥያቄ ። ከመሲሂደጃል ፈተና፡ - ብዙ ሰዎች ተታለው እንደ ጌታ አድርገው እንዲከተሉት ምክንያት ከሚሆኑት ተዓምራቶቹ።

**ጥያቄ፡-** ውየው በመስገድ ላይ እያለ ከነሰረው ሕክሙ ምንድን ነው? ልብሱስ ይነጀሳልን?
**መልስ፡-** ነስር ብዙም ይሁን ትንሽ ውዱእ አያፈርስም። እንደዚሁም ከሁለቱ መንገዶች (ከፊንጢጣና ሽንት መሽኛ) ውጭ የሚወጣ ማንኛውም ነገር ውዱእ አያበላሽም። እንደ ሚያበላሽ ከነብዩ ﷺ የተዘገበ ነገር የለምና። "አስሉ" (መሰረቱ) የጡሃራ መኖር ነው። ይህ ጡሃራ (ውዱእ) የፀናው ሸሪዓዊ ማስረጃ በሚያመለክተው መሰረት ነው። በሸሪዓዊ ማስረጃ የፀና ነገር ደግሞ በሸሪዓዊ ማስረጃ እንጂ ውድቅ ሊሆን (ሊፈርስ) አይችልም። ከሁለቱ መንገዶች ውጭ የሚወጣ ነገር ወዱእ ለማፍረሱ ደግሞ ማስረጃ የለም። ስለዚህ ነስር ወይም ትውከት ብዙም ሆነ ትንሽ ውዱእ አያፈርስም። ነገር ግን ሶላት ውስጥ የሚረብሽህና የሚያስቸግርህ ከሆነ ወይም ሶላትን በ‹ኹሹዕ›ና በእርጋታ ለመፈፀም የማያስችልህ ከሆነ ሰላቱን አቋርጠህ መውጣትህ ችግር የለውም። መስጊድ ውስጥ ከሰገድክና ነስሩ ወይም ትውከቱ መስጊድ የሚያበላሽ ከሆነ ደግሞ አቋርጠህ የመውጣት ግዴታ አለብህ። ከዚህ የነስር ደም ልብስ የሚነካው ትንሽ ከሆነ ልብስን አይነጅስም።
**ጥያቄ፡-** እየሰገድኩ ሳለሁ ጥያቄ ብጠየቅ እና ለዛ ጥያቄ በምልክት መልስ ብሰጥ እንዴት ይታያል ? ለምሳሌ እየሰገድኩ ከኋላይ እኔን ለመከተል ያፈለገ ሰው መጥቶ ሱና እየሰገድክ ነው ብሎ ቢጠይቀኝ በጭንቅላቴ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ መስጠት እችላለሁን?
**መልስ፡-** በሶላት ውስጥ ሆኖ ማመላከት ይቻላል። ምንም ችግር የለውም። ሶላትንም አያበላሽም። የፍጡራን ሁሉ መሪ እና አስተማሪ የሆኑት መልዕክተኛችን ﷺ ተግብረውታልና። የሳቸው ባልደረቦችም ተጠቅመውበታል። ልጠብቅህ ብሎ ቢጠይቅህ አንተ በሶላት ውስጥ ሆነህ ለዚያ ምላሽ በጭንቅላትህ ብታመላክት ምንም ችግር የለውም። ወይም የሆነ ጥያቄ ብትጠየቅና አዎ ወይም አይደለም ብለህ በምልክት መልስ ብትሰጥ ስህተት አልሰራህም። መልዕክተኛውም < ተግብረውታልና። ሰላምታንም ቢሆን በምልክት መልሰዋል።
**ጥያቄ፡-** ወደ መስጊድ ስገባ ሶላት ተጠናቆ አንድ ሰው እየሰገድ አገኘሁት። የሚሰግደው ፈርድ ይሁን ሱና ማወቅ አልቻልኩም ምን ማድረግ አለብኝ?
**መልስ፡-** ጠይቀ'ነው በምልክት እንዲነግርህ ማድረግ ትችላለህ። ዝም ብለህ ተከትለ'ነው ብትሰግድም ችግር የለውም። እየሰገደ ያለው ሱና ከሆነ ሲጨርስ አንተ የቀረውን ትሞላለህና።
**ጥያቄ፡-** አንድ ሰው ለሶላት መስጊድ ሲገባ ሶፉ ሞልቶ ቢገጥመውና ከኋላ ህጻናት ብቻቸውን እየሰገዱ ቢሆን ምን ማድረግ አለበት? ብቻውን ከኋላ መቆም ወይስ ከህፃናት ጋር መስገድ?
**መልስ፡-** ሰጋጁ መስጊድ ሲገባ ሶፉ ሞልቶ ከሆነ በሶፎች መሀል ለሱ የሚበቃ ቀዳዳ ያገኝ እንደሆነ ይፈልግ። ወይም የሚመች ከሆነ ከኢማሙ በቀኝ ጎን ቆሞ ይስገድ። ይህን ካልቻለ ሌላ አብሮት የሚሰግድ ሰው እስኪመጣ መጠባበቅ አለበት። ብቻውን ከሶፍ ኋላ ቆሞ መስገድ አይችልምና። ህጻናቶቹ ከሰባት አመት በላይ

ከሆኑ ከነሱ ጋር መስገድ ይችላል። ከዚያ በታች ከሆኑ ግን ብቻ ከመስገድ አይለይም። መልዕክተኛው ﷺ «ከሶፍ ኋላ ብቻውን ቆሞ የሚሰግድ ሶላቱ ትክክለኛ አይደለም።» በማለታቸው ሶላቱ ተቀባይነት የለውም።

**ጥያቄ፡-** አንድ ሰው መስጊድ ሲገባ ሶፉ ሞልቶ አገኘው። ሊያስገባው የሚያስችል ክፍት ቦታ አላገኘም ከኢማሙ በቀኝ ጎን ለመስገድም አልተመቸውም። ሶላቱ ደግሞ እያመለጠው ነው ። ከሶፍ ኋላ ቆሞ ብቻውን መስገድ አለበት ወይስ ፊት ለፊት ካለው ሶፍ አንድ ሰው ጎትቶ አብሮት መስገድ አለበት?

**መልስ፡-** ሁኔታው በጥያቄው እንደተገለጸው ክፍት ቦታ ካላገኘና ከኢማሙ በቀኝ ጎን መስገድ ካልቻለ ሶላቱ እየተጠናቀቀ ቢሆንም እንኳ አብሮት የሚሰግድ ሰው ይጠብቅ። ካላገኘ ኢማሙ ሶላቱን ሲጨርስ ሌላ ጀምዓ ጠብቆ ይስገድ። ሌላ ጀምዓ ካላገኘም ለብቻው ይስገድ። ምንም ወንጀል አይኖርበትም። አላህ በአቅማችሁ ያህል ፍሩኝ ብሏልና። መልዕክተኛውም ﷺ ኢማሙ አህመድ በዘገቡት ሀዲስ «የዘዝኳችሁን በአቅማችሁ ያህል ተግብሩት።» ብለዋል።

ሶላት ኢባዳ እንደመሆኑ በታዘዝነው መልኩ ነው መተግበር ያለብን። ከሶፍ ኋላ ብቻ ቆሞ መስገድ የሚከለክለው ሀዲስ ሶሂህ (ተቀባይነት ያለው) ነው። ሰውን ጎትቶ መስገድ የሚፈቅደው ሀዲስ ደግሞ ዶኢፍ (ተቀባይነት የሌለው ደካማ) ሀዲስ ነው። እንጠቀምበት እንኳ ብንል ከፊቱ ሶፍ ሰው ስንጎትት በሶፉ ላይ ክፍተት ይፈጠራል። መልዕክተኛው ﷺ ደግሞ ሶፍን እንድንሞላና ክፍተትን እንድንዘጋ ነው ያዘዙን።

**ጥያቄ፡-** ከመስኪድ ውጭ ለምሳሌ ከመስኪድ ጋር በተገናኙ መንገዶች ላይ የሚሰግዱ ሰዎች ሑክም ምንድነው?

**መልስ፡-** መስኪድ ለሰጋጆች የማይበቃ ከሆነና ከመስኪድ ጋር በሚገናኙ መንገዶች ላይ ቢሰግዱ ኢማሙን መከተል እስከቻሉ ድረስ ችግር የለውም። ኢማሙን መከተል ግዴታ ነውና።

**ጥያቄ፡-** ደም ሳያቋርጥ የሚፈሳት ሴት እንዴት ነው የምትሰግደው?

**መልስ፡-** ደም ሳያቋርጥት የሚፈሳት ሴት በተለምዶ የወር አበባዋ የሚቆይበት ግዜ ያህል ሳትሰግድ ትቆያለች። ለምሳሌ፡- በተለምዶ የወር አበባዋ ሁሌም በወር መጀመሪያ መጥቶ ለስድስት ቀን የሚቆይ ከሆነ እሷም ሁሌም በወሩ መጀመሪያ ላይ ለስድስት ቀናት ሳትሰግድ ትቆያለች ። ስድስቱን ቀን ስትጨርስ ታጥባ ሶላታን ትሰግዳለች።

ይህች ሴት እና መሰሎቿ የሚሰግዱበት ሁኔታ፡- የፈርድ ሶላት ወቅት (ጊዜ) ሲገባ ብልቷን በደንብ ታጥብና በጥጥ ወይም በጨርቅ ሸፍና ታስረዋለች። ከዚያም ውዱዕ አድርጋ ትሰግዳለች። ከፈርድ ሶላት ጊዜ ውጪ ሱና መስገድ ከፈለገችም በእንደዚሁ ሁኔታ ትሰግዳለች ። በዚህ ሁኔታ ከቆየች መቸገሯ ስለማይቀር ዙሁር እና አስርን ፤መግሪብን እና ኢሻዕን እያጣመረች መስገድ ትችላለች ። ማለትም በቀን ውስጥ አምስት ጊዜ ታጥባ ውዱዕ በማድረግ ፈንታ ሦስት ጊዜ ታደርጋለች።

**-ተፈጸመ-**

- إدارة الأوقاف الخيرية

- قسم تطوير المناهج الدّراسية

## عنوان المركز

☏ +251112781893

Fax: +251112779660

E-mail: info@nesiha.org

www.nesiha.org

ADDIS ABABA

ETHIOPIA

- مركز تحفيظ القرآن الكريم (للبنين وللبنات)
- مركز تعليم القرآن الكريم وتربية الأطفال
- قسم كفالة الدّعاة والمدرسين ودعم المدارس وتطوير المناهج الدّراسية
- المكتبة العلميّة العامّة
- مركز الدّعوة عبر الإنترنت
- قسم تعليم الصّم بلغة الإشارة
- قسم تثقيف طلبة العلم الشرعي من خريجي الحلقات العلمية أكاداميا
- قسم عمارة المساجد
- قسم كفالة الدّعاة والمدرسين

وبعون الله تعالى حقق المركز إنجازات مهمّة خلال وقت قصير بتخطيط استراتيجية عامّة للدّعوة محورها الأساسي نشر الدّين بمفهومه الصّحيح والدِّفاع عنه والتصدي للأفكار الهدامة، ويعلوها نشر العلم الصّحيح المستمد من الكتاب والسنّة على فهم سلف الأمّة بوسائل مختلفة وفي مناطق متفرقة في البلاد.

## أقسام المركز

يشمل المركز عدّة أقسام منها:-

- مركز الهِداية لتعليم المهتدين الجدد
- معهد اللغة العربية والعلوم الشّرعيّة للبنات
- معهد دار الحديث لتدريب الدّعاة والمدرسين

# نبذة تعريفية عن مركز ابن مسعود الإسلامي

## بسْمِ اللهِ الرَّحمَنِ الرَّحِيمِ

الحمد لله رب العالمين، وصلى الله وسلم وبارك على محمد وعلى آله وصحبه، أما بعد:–

أُنشِئ مركز ابن مسعود الإسلامي في شهر شعبان سنة 1430 هـ بعد ماحصَل على شهادة الرّخصة كهيئة دينية من وزارة العدل الإثيوبي برقم 0034 تمكّنه من القيام بأنشطة دعويّة تخدم الإسلام والمسلمين بطرق منتظمة في مجالات كثيرة. فهو حافل بأنشطة علميّة مختلفة من الدّروس والمحاضرات والأنشطة الثقافية والندوات والمسابقات الدّينية والدّورات العلميّة وغيرها.

ለተሟላ ጥቅም ይህንንም ያንብቡ!!!

# ጥሪ ወደ ሶላት!!!

*ሀዮ አለ ሶላህ!!!*

ዝግጅት፦ ኻሊድ አቡ ሷሊህ

ትርጉም፡- ኒዛሙዲን አወል (አቡ አይመን)

حيّ على الصلاة

إعداد: خالد أبو صالح

ترجمة: نظام الدّين أوّل

أمهري – إثيوبيا